# ኢየሱስም መጣና ጠራ

ቅዱስ ዮሐንስ፡ ምዕራፍ 11፡ ከ18ኛው ቁጥር ጀምሮ፡ ማንበብ እፈልጋለሁ።

**ቢታንያም እሥራ አምስት ምዕራፍ ያህል ለኢየሩሳሌም ቅርብ ነበረች፡**

**ከአይሁድም ብዙዎች ስለ ወንድማቸው ሊያጽናኑአቸው፡ ወደ ማርታና ወደ ማርያም መጥተው ነበር።**

**ማርታም፡ ኢየሱስ እንደ መጣ በሰማች ጊዜ፡ ልትቀበለው ወጣች፡ ማርያም ግን በቤት ተቀምጣ ነበር።**

**ማርታም ኢየሱስን፡ ጌታ ሆይ፥ አንተ በዚህ** ኖረህ **ብትሆን ወንድሜ ባልሞተም ነበር።**

**አሁንም ከእግዚአብሔር የምትለምነውን ሁሉ... እግዚአብሔር፡** እንዲሰጥህ፡ **አውቃለሁ አለችው።**

**ኢየሱስም፡ ወንድምሽ ይነሣል** አላት።

**ማርታም፡ በመጨረሻው ቀን በትንሣኤ እንዲነሣ አውቃለሁ** አለችው።

**ኢየሱስም፡ ትንሣኤና ሕይወት... እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ፡ ቢሞት እንኳ፡ ሕያው ይሆናል፤**

**ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም፤ ይህን ታምኚያለሽን አላት?**

**እርሰዋም፡ አዎን ጌታ ሆይ፤ አንተ፡ ክርሰቶስ የእግዚአብሔር ልጅ፡ እንደ ሆንህ እኔ አምናለሁ** አለችው፡ **ወደ ዓለም የሚመጣው እንደ ሆንህ አምናለሁ።** (ከዛ ይሄን ተመከቱ!)

**ይህንም** ብላ፡ **ሄደች፡ እኅትዋንም ማርያምን በሰውር ጠርታ፡ መምህሩ መጥቶአል፡ ይጠራሽማል፡ አለቻት።**

2 እንጸልይ። የሰማይ አባት ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ እኛ አንተን ስንጠባበቅ፡ እነዚህን ቃላት በልባችን ውስጥ አትም። ቃልህ፣ ባርያህ፣ እና ርዕስ ጉዳዩ፡ በኢየሱስ ክርሰቶስ ሰም፡ ለአንተ አሳልፈን ሰጠንህ። አሜን።

አረፍ በሉ።

3 ወደዚህ የመምጣቴ አላማ የጌታን ህዝብ ለመርዳት በማሰብ ነው። በሽተኞች ላይ እጅ እሰከ መጫን እና፡ እሰከ መጸለይ ብቻ ሳይሆን፡ ኢየሱስ ክርሰቶስ ከኛ ጋር መሆኑ፡ የእግዚአብሄር ልጅ ከኛ ጋር እንዳለ ማወቅ እንዲችሉ ነው። **ኢየሱስም መጣና ተጣራ**፡ በሚል ርዕሰ ጉዳይ ዛሬ ማታ እንነጋገራለን።

4 ይህ አሁን የምናወራበት ወቅት፡ እጅግ ሀዘን የነበረበት ወቅት ነው። የጌታችን የህይወት ታሪክ በተመለከተ ካነበባችሁ፡ አልዓዛር ለተባለው ለዚህ ወጣት፡ የቅርብ ወዳጅ እንደነበረ እናያለን። ከ... ዮሴፍ ሞት በኋላ፡ ማለት፡

ከማርታ፣ ማርያም፣ እና ከአልዓዛር ጋር ለመኖር ለቆ መጥቶ ነበር። ስለዚህ የቅርብ ጓደኞቹ ነበሩ። ማለት... እውነኛ ወዳጅ—ልክ እንደ ፓስተራቸው ነበር። የሚለበስ ያዘጋጁለታል፡ የሚለበስ ኮት፡ ልብሱም ስፌት ሳይኖረው የተሸመነ፡ እንደሆነ፡ ይነገራል። ተከታዮቹ ስለነብሩ፡ ብዙ ነገሮች ያደርጉለት ነበር። እሱን ለመከተል፡ አምነው—አይተውታል። ቸርቻቸውን ትተው ወጥተዋል፡ ስለሱ ብዙ ነገር አርገዋል። በዚያ ዘመን ይህ ቀላል አይደለም፡ ከነዚያ—መለየት ማለት፡ እስከ ሞት ድረስ የሚያስቀጣ ነበር።

5 እና፡ ምኩራቦቻችን እያፈረሰ ከቦታ ቦታ ይዞራል የሚሉት፡ ይህ ኢየሱስ፡ ስለ ካህናቶቻችን ክፉ ነገር ያወራል፡ እንዲህ— እና እንዲያ ያደርጋል፡ እሱ—በእኛ ላይ ብዙ ጉዳት አድርሷል፡ ይሉታል። እና—ሰሙ መጥራት በራሱ—ከምኩራቦቻቸው የሚያስባርር ነበር። ከቤተ—ክርስትያናቸው እንዴ ከወጣችሁ—ለቤዛነት ሌላ ዕድል የለህም፡ ብለው ያስባሉ። እንደ ፈሪሳውያን፣ ሶዱቃውያን፣ ወይም እነሱን ከሚመስሉ ሌሎች አንዱ ካልሆናችሁ፡ ከነዚህ ውጪ ከሆናችሁ ቤዛነት የለም። እና ፍቃድ ካገኙ፡ ቁልፍ ከያዙ፡ እንደፈለጉ ሊያባርሯችሁም ይችላሉ። ይህ ነበር የሚሉት። ኢየሱስም፡ "እናንተ፡ ስለ ባህላችሁ፡ የእግዚአብሄር ቃል ከንቱ ታድረጋላችሁ" ማለቱ ልክ ነበር። አያችሁ?

6 አሁንም እንደገና ተደገመ፡ ምክንያቱ ብዙ ጊዜ ታሪክ እራሱን እንደሚደግም እናውቃለን። ይህ—ማለታችን ያሳዝናል፡ እንደሚደገም ትንቢት ስለነበረ ግን፡ አሁን እንደገና ተፈጸመ።

ኢየሱስ በደንብ ተቀባይነት ያላገኘ ሆኖ እናገኘዋለን።

7 ብዙ ግዜ፡ ሰዎች ከእነሱ ጋር ያልተሰማማ ሰውን መፍረድ ይወዳሉ። እኛ ግን እንዲህ እናደርግም። አንዳችን ከሌላው ላንሰማማ እንችላለን፡ ነገር ግን በመዋደድ ይሁን። እየወደድኩት እና እየጸለይኩለት፡ ከአንድ ሰው ጋር ባልሰማማ፡ እና ከዚህ ሰው ጋር፡ በቅዱስ ቃል ምክንያት-... እና ለተሻለ አብርሆት ከሱ ጋር ባንሰማማ፡ አንዳች ነገር ልለው አይገባኝም። ስለምወደው፡ እና—እንዲጠፋ ስለማልፈልገው፡ ከሱ ጋር መሰማማት ባልፈልግ እንኳ፡ በፍቅር ነው። እሱም በእኔ ላይ ተመሳሳይ ነገር ማድረግ አለበት፡ መጥፋት የለብንም። መነሻችን ቃሉ በሚለው መሰረት ማድረግ አለብን። ቃሉ እውነት ይሁን። በእኛ መመርያ እና ሐሳብ ሳይሆን፡ ወይም በግል ትርጓሜ ሳይሆን፡ እሱ በሚለው፡ ማለት ቃል በሚናገረው መሰረት።

8 በቀደምለት ማታ ላይ፡ አንድ ነገር አደረግኩ፡ ነገርየው ሐጥያት ይመስላል፡ የአገልጋዮች ቁርስ በነበረ ጊዜ ባለፈው ጠዋት ይመስለኛል። ኢየሱስን በፍርድ ፊት አቀረብኩት። "ያኔ ያደረጉት፡ አሁንም ያደርጉታል።" አልኳቸው። እስኪ ምናልባት ጊዜ ካለን፡ ለአፍታ ያህል አሁን ደግሜ ባቀርበው ጥሩ ይመስለኛል። አሁን፡ ቅድም እንዳልኩት፡ ዛሬ ይህን እውቀናል...

9 በሉተር የተሀድሶ ዘመን፡ እሱ፡ በዚያን ዘመን፡ ጻዲቅ በእምነት ይኖራል አለ። "ይህን፡ የሚሞላ ሰው፡ የሚያምን ሰው ነው።" ብዙዎች አምኛለሁ ሲሉ እናያቸዋለን፡ ነገር ግን አልተሞሉም።

10 በጆን ዌስሊ ዘመን—ሁለተኛው ጸጋ፡ ሲቀበሉ፡ ቅድስና፡ ይሉታል፡ ሙሉ ቅድስና ሲቀበሉ፡ ደስ ይላቸዋል ይጮኻሉ። "ሁሉም፡ ተሞልቻለሁ ብለው

ይጮኻሉ።” እንዳልተሞሉ ግን ይደርሱበታል። ብዙዎቹ ይጮኻሉ፡ ግን አይሞሉም።

11 በጴንጤቆስጤ ዘመን፡ እንዲህ አሉ፦ “የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ የጸጋ ስጦታ መቃናት ተለቋል። በልሳን የተናገረ፡ ተሞልቷል አሉ።” ብዙዎች በልሳን ሲናገሩ አይተናቸዋል፡ ነገር ግን አልተሞሉም።

12 እና “አዎን፡ የመንፈስ ፍሬ፡ ይህ ነው” አሉ። አይይ፡ አይደለም፡ የመንፈስ ፍሬ ይሄ አይደለም። ያንን′ማ ክርስትያን ሳይንሶችም፡ በደንብ አላቸው... የመንፈስ ፍሬ ማለት ግን ፍቅር ነው። ከዚያም፡ ከሌላው ሁሉ ይልቅ ፍቅር ይኖራቸዋል፡ የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት ግን ይክዱታል፡ ነብዩ ብለው ይጠሩታል፡ ተራ ሰው ያደርጉታል። አያችሁ? ይሄም አይሰራም።

13 እንደው አንድ ደቂቃ ብቻ ይሄን ጥያቄ ውስጥ ላስገባው። እስኪ ኢየሱስን ፍርድ ፊት እናቅርበው። ብቻ ከዚህ መድረክ፡ እንዲህ ማሰቤ እግዚአብሄር ይቅር ይበለኝ። ነገር ግን እናንተን ወደ ብርሃን ለማምጣት፡ እስኪ ለአፍታ ያህል፡ ልቃወመው። አያችሁ?

14 “ዛሬ ማታ፡ የምናገራቸው እናንተ ሰዎችን አግኻቻለሁ። እኔ... ” (የናዝሬቱ ኢየሱስ በምድር የነበረው፡ ድሮ በሌላ ዘመን ነው።) “አሁን ግን ይህን የናዝሬቱ ኢየሱስ የተባለው ሰው ለመቃወም፡ እና ለመመገት፡ ወደ እናንተ መጥቻለሁ። እግዚአብሄር ፍቅር እንደሆነ ሁላችንም እናውቃለን። መጽሐፍ ቅዱስም ነው ይላል። በጣም ጥሩ፡ ፍቅሩ መንፈሱ፡ ትዕግስት፣ ራስን መግዛት፣ በጎነት፣ የውሃት፣ ፍቅር፣ እና ሌላም ነው። አሁን፡ አንድ ነገል እጠይቃቸዋለሁ ብያለው። እንደ ክርስትያን፡ የምናውቀውን—እንመርጣለን።

15 “ሽማግሌው ካህናችሁን ተመልከቱት። ቅመ-ቅመ-ቅመ-ቅድመ አያቱ ካህን ነው። ካህን ለመሆን፡ በሌዊ የዘር ሐረግ መወለድ ይኖርበታል። አሁን፡ እንደምናውቀው፡ እንደሌሎቻችሁ የወጣትነት ጊዜ የለውም። ምን ሲያደርግ? የእግዚአብሄር ቃል ለማጥናት፡ እራሱን ይሰዋል፡ በእግዚአብሄር ቃል ሁሌ ይዘጋጃል። ቀን ሌሊት፡ ቀን እና ሌሊት፡ ያነበዋል፡ በብራና ውስጥ ያለውን ቃል ሁሉ፡ ፊደል ሁሉ ማወቅ አለበት። በልቡ መያዝ አለበት። ማወቅ እንዳለበት የሚገፋው፡ አንዳች ነገር—አለው።

16 “ሌላ ደግሞ፡ በተጨማሪ፡ እናትና አባታችሁ ሲጋቡ፡ ባል እና ሚስት እንዲሆኑ ያስተሳሰራቸው ማን ነው? ቅዱስ የሆነው ካህናችሁ። አባታችሁ ሲቸገር እርዳታ ሲሻ እርሻው በብድር ሲያዝበት የሚመጣለት ማን ነው፡ አበዳሪ ሲመጣበት ማን ይመጣለታል? ከጎኑ ማን ይቆማል? በጎ የሆነው ካህናችሁ። እናታችሁ በክፍሏ እናንተን ስትወልድ ከጎኗ ማን ይቆማል? በጎ የሆነውን ካህን። እናንተ ስትታመሙ እና ስታጡስ ማን ይደርስላችኋል? በጎ የሆነውን ካህን። በስምንተኛው ቀናችሁ ባርኮ ለእግዚአብሄር ሰጥቶ፡ የሚገርዛችሁ ማን ነው? በጎ የሆነውን ካህን። እናት አባታችሁ ሊፋቱ ጫፍ ደርሰው፡ ማን ያስታርቃቸዋል፡ ማን አንድ ያደርጋቸዋል? በጎ የሆነው ካህናችሁ። በመንደራችሁ ችግር ሲነሳስ፡ ማን ይፈታዋል? በጎ የሆነው ካህናችሁ። በትክክል።

17 “አሁን ይህ በጎ ካህን እግዚአብሄር ስለ መስዋዕት ጠቦት እንደሚጠይቅ ያውቃል። እናንተም ብዙዎቻችሁ ነጋዴዎች ናችሁ፡ በጎችን አታረቡም፡

እግዚአብሄር ግን በግ ይጠይቃል። ነጋዴዎች መጥተው እንዲገዟቸው—በጎቻቸውን የሚሸጡበት፡ በግ ተራ አዘጋጅተዋል፣ ይህም እግዚአብሄር የሚጠይቀው መሰዋዕት፡ ስለ ነፍሳቸው እንዲያቀርቡ ነው።

18 "ይህ ኢየሱስ የሚሉት ወጣት ሰው፡ ከየት መጣ? ምንስ አደረገ? በድንግልና፡ ተወልደኩ ይላል። ይህን ትርጉም አልባ ቀልድ የሰማ ማን ነው? እናቱ ከዮሴፍ ከመውለዷ በፊት እንደወለደችው፡ ወይም፡ ከዮሴፍ ጋር ከመጋባታቸው በፊት እንደተወለደ፡ እኛ እናውቃለን። ሲጀመርም፡ እሱ—መጥፎ ስም እንዳለው እናውቃለን።

19 "የየትኛው ህብረት አባል ነው? ይህ ሰው የእግዚአብሄር ሰው ከሆነ፡ ህብረቱ ከእነ ማን ጋር ነው? ካህናችሁ'ኮ፡ ቃልን ለማወቅ፡ ተምሮ፣ ተምሮ፣ ተምሮ፣ ተመራምሯል፡ ይሄኛው መጣና፡ የገነባውን ሁሉ ናደበት። 'እግዚአብሄር' ነው ትሉታላችሁ ወይ? በፍጹም አትሉትም።

20 "አሁን፡ በቀደም ለት ካህናችሁ፡ ሰፍራውን፡ ያንን... እናንተ ሄዳችሁ መሰዋዕታችሁን የምትገዙበት ቦታ ባዘጋጀ ጊዜ፡ ወጣቱ ሰውየ መጥቶ ምን አደረገ? ቸርነት አረገን? ጥቂት ከተልባ እግር እና ከቆዳ ጅራፍ ሰርቶ፣ ገመድ ገመደና፡ ህዝቡን፡ በቁጣ ተመለከታቸው፡ ገረፋቸው፡ ጠረጴዛዎች ሁሉ ገለባብጦ፡ ገርፎ አባረራቸው። ታድያ ሰዎችን፡ በቁጣ የሚያይ፡ የመንፈስ ፍሬ ነው ትሉታላችሁን? እና፡ ተመከቱ፡ ይህ ሰው ያህዌን ከማምለክ ሲወገዝ! ነጋዴው እሱን ማምለክ ፈልጓል፡ የበግ ጠቦት ሰለማያረባ ግን፡ ሊገዛ ወደዚያ ሄደ። ይሄኛው ግን አባረራቸው፡ መታቸው፡ ገለባበጣቸው።"

21 እስኪ የመንፈስ ፍሬ ያለው የትኛው ነው? እህህ-ህም። እያችሁ? ይሄው ነው። እያችሁ፡ የመንፈስ ፍሬ አይደለም፡ በልሳን መናገር አይደለም፡ መጮኽ አይደለም።

22 እናንተም፡- "ወንድም ብራንሃም፡ ታድያ፡ማሰረጃው ምንድነው ትሉኛላችሁ? ማሰረጃው ምንድነው ብትሉ ግን?" የዘመኑ ቃል በጊዜው ሲገለጥላችሁ ነው።

23 እነርሱም'ኮ መጽሐፍ ቅዱስ ነበራቸው። ያህዌ ይሆናል እንዳለው ሆኗል። ስለዚ ሌላ ትርጉም እያስፈልገውም ነበር። እዚያው ተተርጉሟል። ካህናቶቻችሁ እና፡ ያላቸው ሁሉ ያኔም ነበሩ፡ ሁሉንም ነገር እና ሌላው ሁሉ እንደ ድሮው ነው፡ ቃሉን ግን ማየት አልቻሉም። እሱ ግን ቃሉን ለትውልዱ ህያው እንዲሆን አድርጓል። የትውልዱ ማሰረጃም ይሄ ነው።

24 ሉተር የዘመኑ ማሰረጃ ነበረው፣ ዌስሊም የራሱ ዘመን፣ ጴንጤቆስጤም በዘመናቸው፣ እኛም በሌላ ዘመን ውስጥ ነን። እነዚህ ጥሩ ነገሮች ናቸው። ጣት፣ አይን፣ እና አፍንጫ እንዳለውና፡ ከጊዜ በኋላ ሙሉ ሰው እንደሚሆን፡ ልክ እንደ ጨቅላ ነው። አስቀድሞ ባለ ሙሉ አካል—ሊሆን ይገባዋል፡ ከዚያ በኋላ ይወለዳል፣ ነፍስ፣ ስጋ፣ መንፈስ ይኖረዋል፡ ከቦታ ቦታም ይንቀሳቀሳል።

25 ኢየሱስም፡ እነዚህን ነግሮች፡ እንደተናገረ፡ ለሕይወት የተመደቡ፡ ጥቂት ሰዎች ብቻ፡ እሱን ማየት ችሏል። ታላላቅ ጉባኤዎች አላዩትም፡ የሱ ጉባኤ እንደ ቀያፋ ጉባኤ ሊሆን አይችልም። ለምን ብትል፡ ቀያፋ መላ አገሪቱን በአንድነት ሊጠራ ይችላል። ኢየሱስ ግን ጥቂቶቹን ብቻ ሰብስቦ ጠራ።

ብዙዎች አላወቁትም ነበር። በምድር በነበረ ጊዜ፡ ሺዎች እና ሺህ ጊዜ፡ ምድር ላይ ተመላልሷል፡ በምድር እንደነበረ ግን በፍጹም አላወቁም።

26 አሁንም በድጋሚ እንዲሁ ይሆናል! ለሕይወት ወደ ተጠሩት ይመጣል። ለሕይወት የተጠሩትን ሁሉ ያውቃቸዋል። ይሄን ማቀናጀት የሱ ስራ ነው… ሌላ ነገር አይሰራም።

27 ስለዚህ ከምኩራብ ወጥተው፡ በእሱ ማመናቸው አስተውለናል። ስለ'ሱ በቃል የተነገረለት ሁሉ፡ እሱ እንዲሁ ነበር።

28 እና አንድ ቀን ቤታቸውን ለቆ ሄደና። ሶስት ነገሮችን ላንሣ፡ ኢየሱስ መሄዱ፣ ሞት መምጣቱ፣ እና ተስፋ ሁሉ ማለቁ። ለጥቂት ደቂቃዎች በነዚህ ሶስት ጉዳዮች እናገራለው።

29 ኢየሱስ ሄደ። እሱ ከሄደ በኋላ፡ ችግር ገባ። እሱ ከተዋችሁ፡ እናንተን ወይም መኖሪያችሁን ትቶ ከሄደ፡ ችግር መምጣት ይጀምራል። ኢየሱስ ከሄደ ሰይጣን የተከፈተ በር ያገኛል።

30 እና ለቆ ሄደና፡ እሱ—እንደ ሄደ፡ ወድያው ሞት ገባባቸው። ስለዚህ ኢየሱስ ከተለያችሁ፡ ሞት ይገባል። ከእሱ መለየት ማለት ሞት ነው፡ ስለዚህ ኢየሱስ በተለያቸው ጊዜ ሞት ገባ።

31 አልዓዛርም የሞትን ጥላ አጠላበት። ስለዚህም ይህ የሚያምኑበት እና የሚወዱት ሰው፡ መጥቶ አልዓዛርን እንዲጸልይለት መልዕክት ላኩበት፡ አይተው ጌታን የሚያውቅ እንደሆነ፡ አውቀዋል፡ ማርታም በደንብ ገልጻዋለች፡ "ከእግዚአብሄር፡ የምትጸልየው… " "ከእግዚአብሄር የምትለምነው ሁሉ፡ እግዚአብሄር ያደርግልሃልና።" እግዚአብሔርና እሱ አንድ እንደሆኑ አስተውላለች። የዘመኑ ቃል እሱ ነበረ፡ እሷም ይሄን ታውቃለች። ይሁን እንጂ ሄዷል እሱ የለም ሊያገኙት አልቻሉም፡ እሱን ካገኘች፡ ምን ሊሆን እንደሚችል ግን ታውቃለች። እና ወደሱ ላኩ፡ ከመምጣት፡ ይልቅ ግን፡ እርቆ ሄደ። ደግመው ላኩበት፡ እሱ ግን፡ ከመምጣት ይልቅ፡ ርቆ ሄደ።

32 አንዳንዴ እነዚህ ነገሮች ለምን ሆኑብን ብለን እንገረማለን፡ መጽሐፍ ግን፦ "እግዚአብሔርን ለሚወዱት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ" አይልምን? እሱ የሚሰራው የሚያውቅ ነው። ከዘገየ፡ ችግር የለም። የሚሰራውን እሱ ያውቃልና። በምክንያት ነው።

33 በቅዱስ ዮሃንስ 5:19 ላይ፡ እንዲህ ተናግሮ እናገኘውለን፡ "እውነት፡ እውነት፡ እላችኋለሁ፡ አባት ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ፡ ልጅ በራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም።"

34 እንዲርቅ እና ሳይሄድ ብዙ ቀናት እንዲዘገይ፡ አብ ነግሮታል። እነዚያ ቀናት ካለፉ በኋላ ግን፡ ያኔ የተናገረው ነገር፡ ተናገረ፡ "ጓደኞችን አልዓዛር ተኝቷል" አለ።

እነሱም፡ "አይ፡ ጥሩ ነው" አሉ።

35 እሱም "ሞቷል። ስለ እናንተም በዚያ ባለመኖሬ ደስ ይለኛል፡" አላቸው። ምክንያቱ፡ ማረግ ያለበትን ሊነግሩት ወይም ሄዶ እንዲፈውሰው፡ ሊገፋፉት ይችሉ ነበርና። መደረግ ያለበትን ግን አስቀድሞ አውቋል፡ ስለዚህ አድርግ

የተባለውን፡ ርቆ እንዲቆይ እንደታዘዘ አደረገ። መጥቶም በመቃብሩ ላይ ካስተዋላችሁ። ቤታቸውን መጥቶ ካየ በኋላ ይሄን ገልጿል።

36 ማሰባቸውን አላቆሙም፡ በእያንዳዱ ሰዓት፡- “አሁን ይመጣል ይላሉ። ተስፋ ሁሉ ተሟጧል። አልዓዛር ሞቷል። አሁን ሊመጣ ይችላል። ይመለሳል ይላሉ።” መጨረሻ ላይ፡ ሞተ፡ እስትንፋሱ ወጣች።

37 ወጥተው፡ የሰውነቱ ደም ሁሉ አስወግደው፡ ገነዙት፡ በተልባ እግር ጠቀለሉት፡ ቀመሙት፡ ገንዘው መቃብር ውስጥ አኖሩት፡ መቃብሩም በድንጋይ ዘጉት፡ በዚያ ዘመን የቀብር ሰነ ስርዓታቸው እንዲህ ነበርና። መሬት ላይ፡ ወይም አለት ላይ ይፈለፍሉና፡ ድንጋይ ላዩ ላይ ያኖሩበታል፡ ልምዳቸው ነበር።

38 አንደኛው ቀን አለፈ፣ ሁለተኛው ቀን አለፈ፣ ሶስተኛ ቀን አለፈ፣ አራተኛ ቀን አለፈ፣ ሰውየው በመቃብር ውስጥ መበስበስ ጀምሯል። አፍንጫው ሳይወድቅ አይቀርም። እንደሚመስለኝ፡ ከሁሉ በፊት የሚወድቀው፡ አፍንጫ ነው። እና በሰብሷል። ስጋው—ወደ አፈር፡ ወደ መሬት ተመልሷል፡ ወይም እየተመለሰ ነው። ነፍሱም ከእሱ ወጥታ፡ የአራት-ቀን ጉዞ ተጉዛለች።

39 በዚህ ህይወት፡ የቀረለትን የመኖር ተስፋው ሁሉ፡ አልቋል። ተስፋው ሁሉ ባለቀ ማግሰት... “ምናልባት፡ በመጀመርያው ወይም በሁለተኛው ቀን ይመጣል!” በማለት ጠብቀውት ነበር። የለም። በቃ ሞተ፡ እሱም አልመጣም። ወድያው ተስፋ ቆረጡ።

40 ከጥቂት ቀናት በኋላ፡- “መምህሩ ከደጅ ነው” ሳይሏት አይቀርም። ማርታ ወደ ጎዳናው ብቅ አለች!

41 ለካ ኢየሱስ ተስፋ ሁሉ በጨለመበት ጊዜ መጥቷል። ብዙ ጊዜ አመጣጡ እንዲህ ነው። አያችሁ? ጭልም ባለባቸው ጊዜ ኢየሱስ ወደ ትዕይንት ተገለጠ፡ መጣ።

42 አሁን አስተውሉ፡ መጣና ማርታን ጠራ። የሱ መምጣት ጥቂት ተስፋን ጭሯል። ወጣቱ ቢሞትም እንኳ፡ የሱ መገኘት ግን ተስፋን አምጥቷል።

43 ወዳጆች ሆይ፡ ምናልባት ዛሬ ምሽት፡ በካንሰርና በልብ ህመም፡ ዶክተሩ ተስፋ የቆረጠባችሁ እዚህ ካላችሁ። ምናልባት ሳይንስ ተስፋ የለም ብሏችሁ፡ ወንበር ላይ፡ ሸባ የሆናችሁ ካላችሁ፡ የካልሸየም ክምችታችሁ—አልቆ—አጥንታችሁ—ተወላግዶ፡ ከእንግዲህ ማጠፍ የማይቻል የሆነባችሁ። ወይም፡ ልባችሁ—እጅግ ታማችሁ፡ በዶክተር በየትኛውም ደቂቃ ትሞታላችሁ የተባላችሁ። ኦህ፡ ብዙ ሰዎችም በካንሰር እና በቲቢ፡ ምናልባት የነበራችሁ ተስፋ፡ ዶክተሩ አጨልሞባችሁ ሊሆን ይችላል። በዚህ ሁሉ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ መገኘት እና የመገኘቱ እውቅና፡ እንደገና ተስፋዎችን ያመጣል።

44 አንድ ግለ ሰብ ሊነግራችሁ ይችላል። ምናልባት ከዚህ በፊት እናንተ ሰምታችሁት አታውቁም ይሆናል፡ ግን አንዱ መጥቶ፡- “እኔ የማውቀው ቤተክርስትያን አለ፡ በእግዚአብሄር ያምናሉ፡ ለታመሙ ሰዎችም ይጸልያሉ ሲሏችሁ፡” (አሁን፡ እናንተ ለሞት ተዘጋጅታችሁ የነበራችሁ። አያችሁ?)፡ በፍጥነት ተስፋ መዝራት ትጀምራላችሁ። ሁሌ እንዲህ ነው። ባለቀ ሰዓት ላይ፡ ሁሌ አንድ ሰው የሆነ ነገር ያመጣል፡ ስለ ኢየሱስ ይነግሯችኋል። እና የሱ መምጣት ተስፋን ጫረ።

45 ትላንትና እንዳደረገ፡ ዛሬም እንዲሁ ያድርግልን። ያ የተመሰከረለት ቃል፡ ያለ አንዳች ጥርጣሬ ተገልጦ፡ እና ተረጋግጦ ሰናየው ከአስራ ዘጠኝ መቶ አመታት በፊት የነበረ **ያንን** ኢየሱስ፡ ቀራንዮ ላይ የሞተው፡ በሶስተኛው ቀን የተነሳው፡ ለደቀ መዛሙርቱም ታያቸው፡ ዓይኖቻቸውን ከፈተ፡ ይህን የዘመኑ ቃል ኪዳን የፈጸመ፡ ዛሬ ማታ በመካከላችን እዚሁ አለ፡ ለሰዎች ተስፋ ማምጣት ግዴታው ነው። አዲስ ተስፋን ያበራል።

46 ምናልባት እንዲህ ትሉ ይሆናል፡ "ቤተክርስትያን ከደረቀች ቆየች። ላለፉት—ጥቂት—ወራቶች አንዳች ንጹህ ውሃ አልጠጣንም። ሪቫይቫል አልነበረም። ሰው ሁሉ የደነዘዘ፡ ወይም የሆነ ነገር ይመስላል። ቸርች ሄደን አንድ አዝማች እንዘምራለን፡ ከዚያ—ጥቂት መልዕክቶች ሰምተን እንመለሳለን ትሉ ይሆናል።" በድንገት ግን፡ መድረቅ ሲጀማምረን፡ ወድያውኑ፡ ኢየሱስ ወደ ትዕይንቱ ይገለጥበታል፡ ያነቃቃናል፡ አንዳች አዲስ ነገር ያመጣልናል። ይህ ለማድረግ ሁሌ ዝግጁ ነው። ኢየሱስ በመጣ ጊዜ—አዳዲስ ተስፋዎች ገቡ። መምጣቱ አዲስ ተስፋ አመጣ።

47 የተገለጠው የእግዚአብሄር ቃል እሱ እንደሆነ አውቃለች። ዘመኑን ዋጅታዋለች። ባይሆን ኖሮ፡ ግን፡ በኦርቶዶክስነቷ በቀጠለች ነበር። የቤተክርስትያኒቱ አባል በሆነች ነበር። እሷ ግን የተሰፋውን ቃል ተረድታዋለች። የተሰፋውን ቃል በእሱ ሲገለጥ አይታለች እሱ ራሱ ህያው ቃል መሆኑ ገብቷታል። ወድያው ይሄን በሰማች፡ ሌሎች ምን ይሉኛል፡ ምን እባላለሁ አላለችም፡ ባላት አቅም ሁሉ ወደ እሱ ፈጠነች። አያችሁ? የተገለጠ ቃል እሱ እንደሆነ አውቃዋለች።

48 የኤልያስ ዘመን ታሪክ ያለጥርጥር አንብባለች። በዚያ ዘመን፡ የተገለጠ የእግዚአብሄር ቃል እሱ ነበር። ነብዩ እንደሆነ፡ የእግዚአብሄርም ቃል ወደ ነብዩ እንደሚመጣ ገብቷታል። በዚያ ዘመን እሱ በባረካት በረከት ልጅ ያገኘች አንዲት ሴት ነበረች ነብዩ በባረካት በረከት፡ ልጅ ወለደች።

49 አንድ ቀን ግን፡ ወደ አስራ አንድ ሰዓት ገደማ፡ የጸሐይ ምች መታውና። መጽሐፍ ቅዱስ፡ የጸሐይ ምች አይልም፡ ብቻ ከአባቱ ጋር በእርሻው ላይ ነበር። ከቀኑ አስራ አንደኛው ሰዓት ላይ፡ "እራሴን! እራሴን!" ማለት ጀመረ። አባቱም፡ አገልጋዩን፡ ወደ ቤት ውሰደው አለው። ከሰዓት እስኪሆን ድረስ፡ በእናቱ ጭን ላይ ተኝቶ ቆየ፡ በስተመጨረሻው ግን ሞተ።

50 አሁን፡ ጎረቤት ሁሉ መጣና ተንጫጫ፡ ወዲያ ወዲህ አለ... እሷ ግን ተስፋ ከመቍረጥ ይልቅ፡ የተረጋጋች እናት፡ ልጇ ሞቷል፡ ህጻኑን ለነብዩ ብላ ወዳዘጋጀችው ክፍል ወሰደችው፡ በአልጋውም ላይ፡ **እንዲህ** አርጋ አጋደመችው። አገልጋዩንም አለችው፡- "በቅሎ አሰተካክልልኝና፡ ወደፊት ጋልብ፡ ካላዘዝኩህ በቀር እንዳታቆም።" ኦህ፡ ማይ! ይሄ'ኮ ነው!

51 ለክርክር እና ለጭንቀት ጊዜ የለንም። ቀኑ እያለቀ ነው። መድረስ አለብን። እንሂድ። የጎደለን ነገር አለ።

52 እሷም፡- "ወደ ፊትህ ሂድ፡ ካላዘዝኩህ በቀር መጋለብህ እንዳታቆም" አለችው። ኤልያስ ወዳለበት ድረስ ተጓዙ።

53 ኤልያስ፡ የእግዚአብሄር ሰው ሆኖ፡ እንደ ክርስቶስ አይደለም፡ ክርስቶስ አምላክ ስለሆነ፡ ሁሉንም ያውቃልና። ኤልያስ ግን ከእግዚአብሄር አንድ ክፋይ

ነው። ስለዚህ በኤልያስ ወስጥ የነበረው ክርስቶስ ነበረ። በዚያ ዘመን የዘመኑ መልዕክት የሆነ የጌታ ቃል ከነብዪው ጋር ስለነበረ፡ የዘመኑ መልዕክት እሱ ነበር።

54 ኢየሱስ የነብያቶች ሁሉ ሙላት ነበር፡ ሌሎቹ ሁሉ ግን እሱን ተረኩ። በቃ። ከዮሴፍ ጀምሮ፡ ከሰላሳው ብር ጀምሮ፡ ክርስቶስን—በየቦታው፡ ተረከ። ሙሴም እንዲሁ!

55 ዳዊት እንደተጠላ ንጉስ፡ በተራራው ላይ ኖረ፡ ስለተጠላም አለቀሰ። ከሰምንት መቶ አመታት በኋላ፡ የዳዊት ልጅ በተራራው ራስ ላይ ቆመ። ያ ማለት በዳዊት ውስጥ የነበረ የክርስቶስ መንፈስ ነው። እሱም… ማይ! የዳዊት ስር እና ዘር ነበር። ስለዚ እንደተጠላ ንጉስ፡ እያለቀሰ፡ ተራራው ላይ ወጥቶ፡ አለቀሰ፡ "እየሩሳሌም፡ ኢየሩሳሌም ሆይ፡ ዶሮ ጫጩቶችዋ እንደምታቅፍ፡ ስንት ጊዜ አቀፍኩሽ።" ይህ ምን ነበር? ያኔም ቢሆን ክርስቶስ እንደነበረ ያሰረዳል።

56 ዳዊት በመዝሙር "አምላኬ፡ ለምን ተውከኝ? ብሎ የጻፈ ጊዜ ሲያለቅስ የነበረው ክርስቶስ ነበር፡ አጥንቶቼ ሁሉ ተቆጠሩ፡ እነርሱም አዩኝ። እግሬን እና እጆቼን ወጉኝ። ልብሴን ቀደዱት። መጎናጸፍያየንም እጣ ተጣጣሉበት።" ክርስቶስ በዳዊት ውስጥ ሆኖ የተናገረው ነው። አዎን። የቃል መገለጥ እሱ ነበር። ቃል በነቢያት ዘንድ ነበረና፡ ክርስቶስ በነቢያት የተነገሩትን ሊፈጽማቸው መጣ።

57 ትናንት ማታ በትምህርታችን ላይ ተናግሯል፡ ቃል ከእነርሱ ጋር ስለነበረ፡ ነብያት ስለሱ የተናገሩትን ሊፈጽም መጣሁ ብሎናል። ኤልያስም የእግዚአብሄር ነብዪ ነበር፡ የዘመኑ ቃል ነበረ።

58 ሱነማዊቷ ሴትም ነብዪው መጥቶ የእግዚአብሔርን ኃይል እስኪገልጥ ድረስ ከዚያ ከእርሱ ጋር ቆየች፡ በሕፃኑ ላይም ተኛበት፡ ሕፃኑም ሕያው ሆነ።

59 አሁን ማርታ ይህን ሳታውቅ አትቀርም፡ ቤትን በማስተካከል፣ እቃ በማጠብ እና የመሳሰሉትን በመንከባከብ የተጠመደች ብትሆንም። እዚያ ግን ቀለሟን አሳይታለች። በእሷ ውስጥ ያለውን በትክክል አሳይታለች። ወዲያው ልትቀበለው ሄደች። እግዚአብሔር በኤልያስ ከነበረ፣ እግዚአብሔር በክርስቶስ መሆን ነበረበት፣ ምክንያቱም እርሱ ያ ሰው መሆኑን ስላረጋገጠ። አሜን። ቁርጠኝነቷ፡ ወደድኩት! ወደ'ሱ ሄደች። ወደ እሱ መሄድ ነበረባት። እና ወደ እሱ እንደደረሰች፡ ነገሩ ገባት—ለእሱ፡ እግዚአብሔር ፕሮግራሙን ፈጽሞ እንደማይለዋወጥ፡ አትርሱ፡ እርሱም እንደማይለወጥ እወቁ። በኤልያስ ሆኖ ሙታንን ማስነሣት ከቻለ፡ በክርስቶስ ሆኖ ሙታንን ማስነሣት ይችላል፡ ባያደርገውም፡ እሱ ራሱ አንዱ አምላክ ነውና።

60 እሱ አሁንም አልተለወጠም! ልክ እንደ ድሮው ዛሬ ምሽትም ያው አምላክ ነው። እሱ ትናንትና፣ ዛሬ፣ እና ለዘላለም ያው ነው። አይለዋወጥም።

61 በሱ እንደሆነም ታውቃለች እሱም ያውቃል። ስለ ወንድሟ የሆነ ነገር በነገረችው ጊዜ፡ ባጭር ደቂቃዎች እንደሚያረጋግጥ፡ ተመልከቱ፡ "ጌታ ሆይ፡ እኔ—አንተን አምንብሃለሁ፡" አለችው።

62 እሱም አላት፦ "ትንሳኤ እና ህይወት እኔ ነኝ። ቢሞት እንኳ በህይወት ይኖራል። ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም። እኔ

ነኝ።" ከሙሴ ጋር፡ በሚነድ ቁጥቋጦ የነበርኩት እኔ ነኝ። "ትንሳኤ እኔ ነኝ። ህይወት እኔ ነኝ። እኔ ግንቡ ነበርኩ። እኔ አሁንም እሱ ነኝ። ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ። በእኔ የሚያምን፡ ቢሞትም እንኳ፡ በህይወት ይኖራል። ሕያው የሆነ የሚያምንብኝም ሁሉ፡ ለዘላለም አይሞትም።" የተሰፋው ቃል እሱ እንደሆነ፡ በዚህ ታላቅ ማረጋገጫ፡ ነብዪ ሆኖ፡ ሊዋሽ እንደማይችል፡ ካረጋገጠላት በኋላ፡ እንዲሁም፡ "እኔ እራሴ እኔ ነኝ። ትንሳኤ እና ህይወት የሆነው እኔ ነኝ፡" ብሎ በነገራት ጊዜ።

63 እንዲህ አለችው፡- "ወደ ዓለም ሊመጣ የሚገባው፡ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆንክ አምናለሁ። ወንድሜ በመቃብር ውስጥ ቢገባ፡ ቢሞት እንኳን፡ ስጋውም... እየበሰበሰ ቢሆንም፡ አሁንም ግን፡ አንተ ያልከው ሁሉ፡ ይሆናል።" አዎን!

64 እሷ የናፈቀችው እሱ ሲናገር መስማት ብቻ ነው! አሜን። ማርታ፡ ሆይ፡ ዛሬ የት ነን? "ቃል ብቻ ተናገር፡ ባርያየ ይድናል!" ሲናገር መስማት ናፍቃለች! ተናግሯል ብለው ሊነግሯት ሊመጡ ይችሉ ነበር፡ ነገር ግን እሱ ራሱ ነበረ። አምላክ ሆይ፡ ያዩ ዘንድ፡ የታወሩ አይኖች ክፈት! እሱ፡ በመገኘቱ፡ ቃል ካወጣ፡ ሁሌ ይፈጸማል።

65 እንዲህ አለች፡- "ከእግዚአብሄር የምትለምነው ሁሉ እግዚአብሄር እንዲሰጥህ አውቃለሁ። ብቻ ልስማህ!" ቃል ሲያወጣ መስማት ናፈቀች። መስማት የናፈቃት ይህ ብቻ ነበር። መሻቷ፡ ቃሉን መቀበል ብቻ ነበር፡ አደርጋለሁ ሲል መስማት ብቻ።

66 እሱም ወድያው ማድረግ ይችል ነበር፡ ነገር ግን፡ አያችሁ፡ አብ ባሳየው ራእይ መሰረት፡ በመቃብሩ አጠገብ መቆም አለበት። ኦህ፡ ማይ! ታገሱ! እግዚአብሄር ነገርን ሁሉ በጎ እያደረገ ነው። በጎ ይሆናል። ወደ መቃብር እስክትደርስ ብቻ ጠብቋት።

67 አስተውሉ፡ ገና ተሰፋ ሁሉ... በጨለመበት፡ ነገር ሁሉ ገና ሳለ፡ እንዲናገር ልታደርገው ትችላለች። ሞቷል፡ በመቃብር ውስጥ በሰብሷል፡ የሷ ግን መሻት አንድ ነው፡ ቃል ብቻ እንዲያወጣ።

68 እሱ፡ "ትንሳኤ እና ህይወት እኔ ነኝ፡" ሲል አምናለች። አምናዋለች። አሁን አስተውሉ፡ እንዲህ ሲናገር ስትሰማው፡ በማይቻለው ማመን ግድ ሆነባት፡- "ትንሳኤ እና ህይወት እኔ ነኝ። የሞተም ቢሆን፡ ሕያው ይሆናል፡ ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም።" "ይሄን ታምኛለሽ? " አላት፡

69 እሷም አለችው፡- "አዎን፡ ጌታ ሆይ፡ አምናለሁ። አንተ ወደ ዓለም የሚመጣው የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንህ አምናለሁ።" ይሄ ተመችቶኛል። ወደድኩት።

70 ይሄን—ከዚህ በፊት ተናግሬዋለሁ። አሁንም ብናገረው ይጠቅማል። ከዚህ በፊት ከአንድ ሴት ጋር ተነጋግረን ነበር፡ ከጥቂት ጊዜ በፊት የጠቀስኩት አንድ ቤተ ክርስቲያን ናቸው፣ አምላክ እንደሆነ፡ በአምላክነቱ አያምኑም፡ ተራ ሰው፡ እና ነብዪ ነበር ይሉታል።

71 በትክክል፡ እንደዛም ነው። እንደዛ፡ ሲደመር አምላክ ነው። አያችሁ፡ እሱ መገለጫ ነበር። ኢየሱስ፡ ወንድ ልጅ የሆነ፡ ሰው የሆነ፡ አካል ነው በእሱ

ውስጥ ግን እግዚአብሄር አደረበት። በውስጡ እግዚአብሄር ነበር። ሰውና-አምላክ ነበር። ሰው ነበረ፡ ቢሆንም ግን በስጋ የተገለጠ አምላክ ጭምር ነበረ። ኢየሱስን ሰናየው፡ እግዚአብሄርን እናየዋለን። እሱ የተናገረው "አባት ሰታዩ... እኔን ያየ፡ አብን አይቷል" አላቸው። ምክንያቱ፡ ጥላው ነበር፡ ምክንያቱ ቃል ነበር፡ አሜን፡ ይህ በመጀመርያ ነበር። አሜን።

72 ነብያትን ሁሉ "አምላክ፡" ብሎ ጠራቸው። ታውቃላችሁ? "የእግዚአብሄር ቃል የሚመጣላቸውን ሁሉ 'አምላክ' ብላችሁ ትጠሯቸዋላችሁና አላቸው። ታድያ፡ 'የእግዚአብሄር ልጅ ነኝ' በማለቴ፡ እንዴት ታወግዙኛላችሁ? "

73 ምክንያቱ፡ ቃሉ ራሱ እሱ እንደሚመጣ ተናግሯል፡ እና ይህው ቃል እንደገና ሲገለጥ ይታያል። ቢሆንም ግን ፈጽመው አያምኑበትም።

74 ይህች ሴትም "እኔ ላረጋግጥልህ እችላለሁ፡" አለችኝ። "አንተ ሰትሰብክ መሰማት እወዳለሁ፡ ነገር ግን እጅግ አብዝተህ የምታደርገው ነገር አለ፡" አለችኝ።

"እሺ፡ ምንድነው? "

"በኢየሱስ አብዝተህ ትመካለህ፡" አለችኝ።

75 "ሲመጣ የሚያገኝብኝ ጥፋት ይሄ ብቻ እንደሚሆን ተሰፋ አደርጋለሁ፡" አልኳት። "የሚገኝብኝ ብቸኛው ጥፋት፡ ይህ እንደሚሆን ተሰፋ አደርጋለሁ፡" አልኳት። እሷም አለች... እንዲህ አልኳት፦ "አሰር ሺ አንደበት ቢኖረኝ እንኳ፡ ሰለሱ ተናግሬ፡ አልጠግብም፡ ኦህ፡ ማይ!"

እሷም፡ "አንተ ግን'ኮ፡ አምላክ ታደርገዋለህ፡" አለችኝ።

76 "አዎን ነው። ካልሆነ፡ ግን፡ አለም ካሰተናገደቻቸው አታላዮች ቁጥር አንድ አታላይ እሱ ነው፡" አልኳት።

"እሱ'ማ ነብዪ ነበር፡" አለች።

77 እኔም፦ "አዎን፡ ነብዪ ነበር፡ የቃል ሙላት የሆነ ነብዪና-አምላክ፡ ነበር አልኳት። ይሄን ያሰባለው—ወይም ነብዪ ያሰባለው ነገር፡ ቃል ወደ ነብዪ ሰለሚመጣ ብቻ ነው። እሱ ግን የቃል ሙላት ነበረው።"

78 እንደገናም እንዲህ አለች፡ "ላረጋግጥልህ እችላለሁ።" "መለኮት አድርገኸዋል፡" አለች።

"አዎን መለኮት ነበር፡" አልኳት።

እሷም "መልኮት'ማ ሊሆን አይችልም፡" አለች።

"ነበረ... ነበር እንጂ፡" አልኳት።

"መጽሐፍ ቅዱስ አምናለሁ ትላለህ፡" አለች።

"አምናለሁ፡" አልኳት።

79 "በል በገዛ መጽሐፍ ቅዱስህ፡ መለኮት እንዳልነበረ፡ አረጋግጥልሃለሁ፡" አለችኝ።

80 "አረጋግጪልኝ። ቃል እውነት እንደሆነ አምናለሁ፡ ሰለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ከተናገረ፡ እኔ አምናለሁ፡" አልኳት።

81 “በቅዱስ ዮሃንስ 11 ላይ፡ ወደ አልዓዛር መቃብር በወረደ ጊዜ፡ አታስታውሰም? ” አለችኝ፡

“በትክክል አስታውሳለሁ፡ እመቤት፡” አልኳት።

82 “እሺ፡ በመንገድ ላይ ሳለ፡ ያኔ፡ አለቀሰ። መጽሐፍ ቅዱስ፡ ‘አነባ’ ይላል፡” አለችኝ።

“አዎን፡ መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል አነባ ይላል፡” አልኳት።

“ታድያ እሱ መለኮት ሆኖ እንዴት ሊያነባ ይችላል? ” አለች፡

“ሰው ስለነበረ፡” አልኳት።

“ሰው እና መለኮት? ”

83 እኔም፡- “አዎን፡ እመቤት። ከሚያለቅሱ ጋር—እያለቀሰ የሚሄድ፡ ሰው እንደነበረ፡ ማየት ተሰኖኛል። አዎን፡ ከሚያዝኑ ጋራ ያዝናል። ሰው ነበር። ይሁን እንጂ፡ ከሲታው አካሉ፡ ቀና አድርጎ፡ ‘አልዓዛር ሆይ፡ ተነሳና ውጣ፡’ ባለ ጊዜ ግን፡ አራት ቀናት በህይወት ያልነበረ ሰው፡ በእግሩ ቆመ። ይህ ከሰው በላይ ነው፡ በዚያ ሰው እምላክ ስለነበረ ነው።” ከእግዚአብሄር በቀር፡ ሙታንን ማን ያስነሳል? ትንሳኤ እና ህይወት እሱ ነው! ትክክል።

84 ያኔ እጅግ ደክሞ፡ ከጀልባዋ የኋላኛው ክፍል ተኝቶ፡ በነበረባት በዚያች፡ ምሽት ላይ፡ በዚያች ሌሊት አሥር ሺህ አጋንንት ሊያሰጥሙት ተማማሉበት፡ እና ትንሿ ጀልባ በማዕበል በተሞላ ባህር ላይ እንደ ጠርሙስ ክዳን ትንሳፈፍ ነበር። ዲያብሎሶቹም “ተኝቷል፡ አሁን አገኘነው። ሁሉንም አንድ ላይ እናሰጥማቸዋለን፡” ብለው አሰቡ። ኦህ፡ ደክሞት፡ ሰው ሆኖ ነበር፡ ከነቃ በኋላ ግን፡ ማዘብያው ላይ ቆመ፡ ቀና ብሎ አይቶ “ሰላም ይሁን፣ ዝም በል” አለ፤ ነፋሱና ማዕበሉም ታዘዙት። ይህ ከሰው በላይ ነው።

85 ቁራሽ እንጀራ ወይም የሆነ ነገር፡ ወይም ከበለሱ ዛፍ ለመብላት ተርቦ፡ ከተራራው በወረደ ጊዜ፡ ሰው ነበረ። አምስት እንጀራና ሁለት አሳ አንሥቶ፡ አምስት ሺህ ሰዎች ሲመግብ ግን፡ በሰውየው ውስጥ እምላክ ነበር። ትክክል ነው።

86 ኦህ፡ ወደ ጥርጣሬ-የማይገባ-ማንም ቢኖር ይሄን ያምናል፡ ገጣሚዎች ሁሉ ያምኑታል። አንዱ እንዲህ መጻፉ አይደንቅም፡

> በህይወቱ አፍቅሮኛል፡ በሞቱም፡ አድኖኛል፡
> ተቀብሮ፡ ሐጢአቴን አራቀ፡
> ተነሰቶ፡ ለዘላለም በነጻ አጸደቀኝ፡
> አንድ ቀን ይመጣል፡ ኦ ድንቅ ቀን!

87 መዝሙሮቹ የማይሸጡ፡ ኤዲ ፔሮነት። አንድ ቀን፡ በመንፈስ ቅዱስ ተነክቶ እየተንቀጠቀጠ፡ ብዕሩን አነሳና፡ የመክፈቻ ሰነ ሰርዓት ላይ ጻፈ፡ ሲጽፍም፡-

> ሁሉም የኢየሱስን ኃያል ሰም ያወድሱ!
> መላእክትም ይሰገዱ፡
> የክብር ዘውድ ይምጣ፡
> ዘውድ ይጫን የሁሉ ጌታ! (ሃሌሉያ!)

88 እሱ እንደነበረ፡ በእርግጠኛነት፡ እናምናለን። አዎን፡ ወዳጄ።

89 ስለዚህ አሁን በዚያ ዘመን ከነበረው ዘመናዊ አስተሳሰብ ይልቅ፡ የማይቻለው ነገር አመነች። ታዲያ እናንተስ አዲስ ህይወትን ለማየት፡ ልዩ ነገር ሲሆን ለማየት፡ በማይቻል ነገር ማመን አይገባችሁም። እሱ ካወቀ… እሷ ቃል እንደሆነ ማወቅ ከቻለች ግን፡ የማይቻለውን ነገር ይፈጸማል፡ ፈጣሪ ስለሆነ፡ በተናገረው ቃል ሁሉ ላይ ይጸናል።

90 "ለሚያምን ሁሉ ይቻለዋል።" ይህም ቃሉ ነው። ነገር ግን የማይቻል ነገር የሚቻለው፡ እግዚአብሔርን እንደ ቃሉ ሲታምኑት ብቻ ነው። አዎን፡ ጌታየ። እግዚአብሔርን እንደ ቃሉ ስታምኑት፡ የማይቻሉ ነገሮች—የሚቻሉ ይሆናሉ። እግዚአብሔር ይሆናል ሲል፡ ቃሉን ወስደህ የማይቻል ነገር ካለ ተመልከት። በእርግጥም ይሆናል።

91 አስታውሱ ግን፡ በዚህ ሁሉ ሳይቀር፡ "ጌታ ሆይ፡ አሁንም ቢሆን፡ ከእግዚአብሄር የምትጠይቀው ሁሉ፡ እግዚአብሄር ይሰጥሃል፡" አለችው። ከአፉ የሚወጣውን ቃል ማግኘት እንደምትችል አውቃለች። ማድረግ የፈለገችውም ይሄው ነው፡ ቃል መቀበል። አዎን፡ እጅግ በጨለመባት ጊዜ ነበር፡ ኢየሱስም መጣና ጠራት። አቤት፡ ያዩት የትንሳኤ፡ ድንቅ ስራ!

የጨለማ ሰአታት የመጡበትን ተጨማሪ እንመልከት።

92 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት ጥንታዊ ነቢያት፡ ኢዮብ የሚባል ሰው፡ በአንድ ወቅት ይኖር ነበር። ታላቅ ሰውም ነበር። ጌታን—እጅግ ይወድ ነበርና፡ እንዴት እንደሚደረግ የሚያውቀውን ነገር ሁሉ ያደርግ ነበር። ሰይጣንም ሊያበጥረው ተመኘ፡ ስለዚህ አንድ ቀን እግዚአብሄርን አለው… ማለቴ፡ እግዚአብሄርም እሱን፦ "ሰይጣን ሆይ፡ ከወዴት መጣህ? " አለው፡

93 "አቤት፡ ምድርን ከላይ-እስከ-ታች እና ወዲያ-እና-ወዲህ ሁሉ ዞርኳት፡" አለው።

94 "ባርያዬ ኢዮብን አየኸውን? በምድር እሱን የመሰለ ሌላ የለም። ፍጹም ሰው ነው፡" አለው።

95 "ኦህ፡" አለ፡ "አዎን፡ ያልሰጠኸው ነገር፡ ያላደረክለት ነገር የለምና፡ በትክክል፡ ልዩ ሰው ነው። አንድ ጊዜ ብቻ ላግኘው፡ ሞገዱን እለዋውጥበታለሁ። ፊትህን፡ እንዲረግም አደርገዋለሁ።"

96 "ይሄን'ማ አትችልም፡" አለው። አማኞቹን ይሄን ያክል ይተማመንባቸዋልና። ለምን? ፍጻሜ የሌለው ስለሆነ። ዘለአለማዊ ነው። መጨረሻውን ከመጀመርያው ያውቃል። ሰይጣን ይሄን ማድረግ እንደማይችል ያውቃል። እሱ ቃል ስለሆነ፡ የኢዮብን መልስ ያውቀዋል።

97 አሁን፡ ኢዮብ፡ ጤናው ተቃውሷል። ሰውነቱ በብጉንጅ ተወሯል፣ ልጆቹን ገድሎ፣ ያለውን ሁሉ እንደወሰደበት፡ አስታውሱ። አጽናኞቹ መጥተው፡ የተሰወረ ሐጥያት እንዳለበት ነገሩት እንጂ፡ መፍትሄ መስጠት አልቻሉም። ሽማግሌው እዮብ ከባድ መጣበብ ውስጥ ገብቷል።

98 ከሁሉ በፊት፡ እስከ ጭንቅ ድረስ መድረሳችሁ ግድ ነው። የጎዳናው የመጨረሻ ጊዜ ላይ መድረሳችሁ የማይቀር ነው።

99 ስለዚህ እዮብ ወደ ጎዳናው የመጨረሻ ምዕራፍ ደረሰ፡ "የተወለድኩባት ቀን የተረገመች ትሁን። በቀን ጸሐይ፣ በሌሊትም ጨረቃ አይብራባት፡ ሰሟም

አይጠራ አለ።” በዚያ ጭንቀት ግን፡ ኢየሱስ ብቅ አለ። ቁልቁል እየና፡ እንዲህ አለ፦ “አበባ፡ እንደ ሰው ሲሞትና፡ በፀደይ ወራት እንደገና ሲበቅል፡ አየሁ። ዛፍ ቢቆረጥ፡ ከውኃ ሽታ የተነሳ እንደገና ያቆጠቍጣል አለ።” የእጽዋት ህይወት ዳግም ሲነሣ አየ፡ ስለ ሰው ግን፦ “ሰው ግን ይሞትና ይጋደማል፡ ነፍሱም ይሰጣል፡ እርሱስ ከወዴት አለ? ” እዮብ መሽምገሉን ያውቃል። ስለዚህ አለ፦ “ልጆቹ ሊያዝኑለት መጡ፡ እሱ ግን እሺ አላለም። አቤቱ፡ ቁጣህ እስኪያልፍ በሸሸግኸኝ ኖሮ፡ በምስጢር እልፍኝህ በመቃብርስ ምነው በሰወርኸኝ። ቀጠሮም አድርገህ ጊዜም መድበህ ምነው ባሰብከኝ። ይቀጥላል... ” እንዲህ እየተናገርን፡ ብዙ ማለት እንችልለን። በጭንቀት ጫፍ ላይ፡ ደርሷል፡ “ምንስ ይሆናል? ቅጠሎች ይወጣሉ፡ ዛፍ ላይ ይመለሳሉ፡ አበቦችም ዳግም ይወጣሉ፡ ሌላው ሁሉ ዳግም ይመለሳል፡ ሰው ግን ይሞታል ነፍሱ ይሰጣል!” እሱ ተጨንቋል። በዚያ ዕድሜ ሆኖ፡ ምን ሊገጥመው እንደሚችል አያውቅም።

100 በተጨነቀ ጊዜ ግን፡ ኢየሱስ ብቅ አለለት። እግዚአብሔር ራሱን ወደ ሰማይ ቀና አደረገለትና፣ ኢየሱስ በመጨረሻው ዘመን ሲመጣ አየ።

101 ሚስቱ “እግዚአብሔርን ሰድበህ ሙት፡” ባለችበት ጨለማው ሰዓት ላይ እንዲህ አለ፦ “አንቺ ሴት፡ እንደ ሰነፍ ሴት ትናገራለሽ። እግዚአብሄር ሰጠ፣ እግዚአብሄር ነሳ፣ የእግዚአብሄር ስም የተባረከ ይሁን” አለ። ሚስቱ በተነሣችበት። ከቤተክርስትያን በተነሡበት። ሰው ሁሉ በተነሣበት።

102 በዚያ በመጨለመበት ሰዓት፡ ወዴት እንደሚቀጥል በማያውቅበት ጊዜ፡ ኢየሱስ መጣለት። ወድያውም አለ፦ “እኔን ግን የሚቢዠኝ ህያው እንደሆነ፡ በመጨረሻም ዘመን በምድር ላይ እንዲቆም አውቃለሁ። ትሎች ይሄን አካል በልተው ቁርበቴም ካጠፉት በኋላ፡ ያኔ በስጋየ ውስጥ ሆኜ፡ እግዚአብሄርን እንዳይ አውቃለሁ።” በዚያ በጨለመበት ሰዓት፡ ኢየሱስ መጣለት። አዎን፡ ወዳጄ።

103 ሙሴ፡ በእስራኤል በጨለማው ሰዓት ለሙሴ፡ መጣለት። በስራ ቦታው ሳለ፡ በዚያ በቍጥቋጦ እግዚአብሄር አገኘውና “እኔ እኔ ነኝ፡” አለው። ወርዶም ኢያኔስ እና ኢያምበሬስ የሱን ስራ ለማስመሰል፡ የሞከሩትን አስመሳይነታቸውን ሁሉ ተዋጋ። በዚያ ሁሉ፡ በእግዚአብሄር ታምኖ ጸና። በመጨረሻም እስራኤልን አሳመነ። በዚህም ወደ ተስፋይቱ ምድር—ለመሄድ፡ ከግብጽ ተነሳ፡ እግዚአብሄር “በዚህ ተራራ ለእኔ ትሰግዳላችሁ፡” ወዳለበት ሰፍራ ወጣ። የእግዚአብሄር ቃል ነበርና። እግዚአብሄር ተናግሯልና! ሙሴ ወደ ተራራው መሄድ እንዳለበት አውቋል። አሜን። ሊገድለው የሚችል ፎርኦን የለም። ሊገድለው የሚችል ዲያብሎስ የለም። ወደ ተራራው እየገሰገሰ ነው። ሊገድለው የሚችል ማንም የለም። አሜን! ሃሌሉያ! መንፈሳዊነት ተሰማኝ። ወደ ተራራው እየገሰገሰ ነው።

104 እኛም ወደ ክብር መንገድ ላይ ከሆንን! የሚያግደን የለም። አይኖርም፡ ወዳጄ። እግዚአብሔር ቃሉን ሊገልጥ ነውና። ምንም ያህል ዋጋ ቢያስከፍል አይገደኝም፡ ምንም ቢሆን፡ እሱ ያደርገዋል። አዎን።

105 በመንገድ ላይ፡ በጉዞ ላይ ነው። በተራራዎቹ መካከል፡ ይሄው ዳርቻው ላይ ደርሷል። ከበስተኋላው የሚያገሳ ድምጽ ይሰማዋል። ምንድነው? የፎርኦን እእላፋት ሰረገሎች፡ ጦር እና ሌላ፡ ታጥቀው፡ ሊረግጧቸውና፡

ሊያሳድዷቸው፡ተከትለዋቸዋል። ከፊቱም ቀይ ባህር፡ ተጋርጦበታል። ምን አደረገ? ጭንቀት ይዞታል-... ተጨንቋል። ህዝቡ ሁሉ እያለቀሱ፦ “አቤት፡ አሁንስ አለቀልን። ፎርኦን ይገድለናል፡ ሰይፎቹም ይቀሉናል። ልጆቻችን በምድረበዳ ይወድቃሉ አሉ።”

ሙሴም በታላቅ ድምጽ “እግዚአብሄር ሆይ!” አለ፡

106 እነሆም ኢየሱስ በመካከል ገባ። ያኔ የእሳት ዓምድ ነበርና። አዎን። ወርዶ በሱና በአደጋው መካከል ቆመ። አሜን። እሱ-መካከለኛችን ነው። ፈጥኖ-ደራሽ ነው፡ አሜን፡ መካከለኛ ነው። እና ቆመ፡ በዚያ እንደቆመ፡ ክፋ ሊያደርጉ በመጡ በግብጻውያን ሰፈር ጨለማ ሆነ። ለነሱ ግን የሚመላለሱበት፡ ብርሃን ሆነላቸው። ኀፋስ በኃይል፡ መንፈስ በጀመረባት በዚያ ሌሊት፡ እሱ ምን አደረገ? በእሳት አምድ አምሳል ተገለጠ።

107 አሁንም ያንኑ የእሳት አምድ እንደሆነ፡ አስታውሱ። አዎን፡ ወዳጄ። በምድር በነበረበት ወቅት፡ “ከእግዚአብሄር ወጥቼ መጥቻለሁ፡ ወደ እግዚአብሄር እመለሳለሁ፡” ብሏል።

108 ከሞት፣ ከመቃብር፣ ከትንሳኤው፣ እና ከዕርገቱ በኋላ፡ ቅዱስ ጳውሎስ፡ በደማስቆ መንገድ ላይ፡ በእሳቱ አምድ ተመታ። ዕብራዊ እንደነበረ፡ አስታውሱ። ባይሆን ኖሮ... በካፒታል ሌተር ኤሎሂምን፡ L-o-r-d፡ “ጌታ ሆይ፡ አንተ ማን ነህ? ” ባላለው ነበር። “እኔ የማሳድድህ አንተ ማን ነህ? ”

“እኔ ኢየሱስ ነኝ፡” አለው።

109 አሜን! ሃሌ ሉያ! እርሱ የመጀመሪያውና የመጨረሻው ነው። እሱ አሁንም ያው ነው። “ጥቂት ጊዜ አለ ከዚህም በኋላ ዓለም አያየኝም፡ እናንተ ግን ታዩኛላችሁ። ከእናንተ ጋር፡ እንዲሁም በእናንተ ውስጥ እሆናለሁ።” ያው የእሳት አምድ፣ በተመሳሳይ ቃል ኪዳን፣ ቃሉን እየገለጠ፣ ያው ያንኑ የሚያደርግ እግዚአብሔር፣ አሜን። “ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ። የነበረውም፣ ያለዉም፣ የሚመጣውም እኔ ነኝ።” አዎን፡ ወዳጄ። አዎን።

“አባቶቻችን በምድረ በዳ መና በሉ።”

110 “እነርሱ፡ ሁሉም፡ ሞቱ። እኔ ግን እኔ ነኝ፡ ነኝ፡” አላቸው። ሙሴ... በሚቃጠል ቁጥቋጦ ውስጥ፣ ያኔ እኔ ነኝ ነው። እርሱ አሁንም እኔ ነኝ እንጂ እኔ ነበርኩ አይደለም፡ እኔ ነኝ ነው፣ ሁሌም፣ አሁናዊ ጊዜ ነው።

111 እዚህ ላይ ሙሴ ወደዚህ ዳርቻ ጥግ እንደተወሰደ እና ክርስቶስም እንደወረደ ተረድተናል። እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ፡ እንዲህ ይላል፡ ያ፣ “ሙሴ—ከግብፅ ውድ ሀብት ይልቅ የክርስቶስ ነቀፋ የሚበልጥ ባለጠግነት አርጎ ቆጠረ ይለናል።” የክርስቶስ ነቀፌታ! ክርስቶስ ከእግዚአብሄር ዘንድ የወጣ ያንን ሎጎስ፡ ወይም ቅባት ነበር። መልአኩም፣ ማንኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢ ያውቀዋል ያ መልአክ ክርስቶስ ነው። እርሱም በዚያም በምድረ በዳ ነበረ፡ ወደዚህ ትዕይንቱም መጣ፡ ይገለጥ ዘንድ በነበረበት መልክ ተገልጧል። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!

112 ዛሬም፡ ራሱ በተገለጠበት በዚያው መልክ፡ ክርስቶስ መጥቷል።

113 አወጣችኋለሁ አላቸው። የገባውን ቃል ለመፈጸም፡ ይሰራ ነበር። በዚያው ለመጽናት መጣ። ከመጣም በኋላ፡ ማርታ ላይ እንዳደረገው፡ ተጣራ። ጠርቶ፦

“ሙሴ፡ ለምን ወደ እኔ ታለቅሳለህ? ህዝቡን ተናገራቸው፡ ወደፊት ሂዱ በላቸው አለው።” በዚያ ጨለማ ሰዓት ላይ፡ ቀይ ባህር ተከፍሎ ተሻገሩ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ለመፈጸም ጉዟቸውን ቀጠሉ። አዎን፣ የሙሴ ጨለማ ሰዓት ላይ፡ ኢየሱስ ብቅ አለ። አሁን ጊዜ አግኝተናል… ሙሴንም ጠራው።

114 ትኩረታችሁን ወደ ሌላ ትንሽ ሰው ልሳበው። ኢያኢሮስ ይባላል። እሱ ሰውር አማኝ ነበረ። ዛሬ በምድር እንደሱ የመሳሰሉ ብዙዎች አሉ። ኢየሱስን ይወዳል። ስለሱ ሲወራ ሰምቷል። በሱ አምኗል። ግን፡ እያችሁ፡ አስቀድሞ እራሱን ወደ ድርጅት ቀላቅሏል። አዎን። እሱ—እሱ—እሱ—እሱ ከዚያ ወጥቶ… ጌታን መቀበል አልቻለም። አምኗል፡ ጌታን መቀበል ግን አልቻለም፡ ስለዚህ ህብረቱ ከማያምኑ ጋር አደረገ። ይሁን እንጂ እሱ እውነተኛ አማኝ ነበር።

115 ታውቃላችሁ፡ አንድ ሰው ወደዚህ ደረጃ ሲደርስ፡ አንዳንዴ እግዚአብሄር ወደ ትዕይንት ያወጣዋል። እውነተኛ ከለራችን፡ ትክክለኛ ማንነታችን የሚወጣው ስንጨነቅ ነው።

116 እና ይህ ሰው፡ ከማያምኑት ወገን ጋር ህብረት አድርጓል፡ ሄዶም ስሙን በመጽሐፋቸው ላይ አስመዝግቧል፡ ወዘተረፈ። ካህን ስለነበረ፡ በዚህ ጠንቅ—ጌታን መቀበል አልቻለም፡ እንጀራውም ስለነበረች አልቻለም። እና ግን፡ በዚህ ሁሉ ኢየሱስን ያምናል።

117 አንድ ቀን፡ ትንሿ ልጁ ታመመች። አቤት፡ የሆነው። ያለጥርጥር፡ ሰውየው፡ ልክ… እንደው፡ ዶክተር ጠርቷል። ሐኪሙ መጥቶ፡ ብላቴናይቱን መርምሯል። ትኩሳቷ ጨምሯል። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ትኩሳት አይሎባታል፡ ወዘተ፡ በመጨረሻም ወደ ሞት አፋፍ ደርሳለች። ጭንቅ ውስጥ ገባ። አንዳች ነገር ማድረግ አለበት። ምን—ምን ማድረግ እንዳለበት አያውቅም። እና አሰበ፦ “ብቻ እሱ የሚገኝበት፡ የት እንደሆነ ልወቅ አለ።” ኒቆዲሞስ በግሉ ለመጠየቅ፡ እንዳደረገ፡ እስኪመሽ ድረስ አልታገሰም። የውሳኔ ጊዜ ነው፡ መወሰን ያለበት ጊዜ መጣበት እና ያኔ ማድረጉ ግድ ነበር።

118 ወንድም፡ እህቶቼ ሆይ፡ አሁንም፡ያው ነው ብየ አሰባለሁ። መወሰን ያለብን ጊዜ አሁን ነው። ለማመን ወይም ላለማመን ጊዜው መጥቷል። ያቺ የመለያ መሰመር ለወንድና ለሴት ሁሉ ትመጣለች። ለልጅ ሁሉ ይመጣል። አንዳንዴ መሰመሯን ካለፋችኋት፡ አንድ ነገር ብቻ ይጠብቃችኋል፡ እሱም ፍርድ ነው፡ በምህረት እና በፍርድ መካከል ስትተላለፉ፡ ያቺ መሰመር ስታልፏት።

119 አስታውሱ፡ እሱ ተጨንቋል። ምን ማድረግ እንዳለበት አያውቅም። ካህናቶቹ ሁሉ ቆሟል፡ አስተማሪዎች ዙርያውን ከበውታል። መላው ጉባኤ አብሮት አለ፡ ሁሉም የብላቴናዋ ሞት እየተመለከቱ፡ እዚያ ናቸው። ዶክተሩም እጆቹን አጣምሮ፡ ከበስተውጭ ቆሟል፡ እጆቹ እየተንቀጠቀጡ፦ “እኔ የማውቀው መድሐኒት ሁሉ ሰጥቻታለሁ፡ ምነው እስከ አሁን ድረሰ… ”

120 እያችሁ፡ ሁሌም የሚሰራው ኢየሱስ ነበር። ኢየሱስ ይሄን የሚያደርግበት ዓላማ ነበረው፡ የዚያን የታናሹን ሰው ከለር ለማውጣት ነው። ከትንሽ ቆይታ በኋላ፣ ትንሽ ጥቁር ኮፍያውን አምጥቶ ሲያጠልቅ፣ የቄስ ቀሚሱን ሲለብስ ይታየኛል።

“ወዴት ነህ? ”

121 “እሰኪ… ወንዙ ዳር ነው ሲሉ ሰምቻለሁ። ልሂድ እና ልፈልገው!” አቤት፡ አቤት! አርቆ ሄደ!

122 በዚያች ጭንቅ ሰዓት ውስጥ፡ መወሰን ነበረበት፡ የቃል መገለጫ እሱ እንደሆነ አውቋል፡ ወይስ ልጁ ትሙት። ካህን ስለነበረ፡ ቃል አንብቧል፡ የእግዚአብሄር ቃል መገለጫ እሱ እንደሆነ ተረድቷል። እግዚአብሄር በክርስቶስ ሆኖ፡ ዓለምን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበር። ያውቃል፡ ስለዚህ ወደዚህ ጉዳይ እንዲገባ ተገደደ። አንዱ ላይ መውደቅ አለበት፡ ልጁ ትሙት፡ ወይስ ጌታ ይቀበላል። በዚያ አይነት ጭንቀት በደረሰ ጊዜ፡ ኢየሱስ ብቅ አለ። ወደ’ሱ ሄደ። እንዲህ አለ—እንዲህ፡ “ስላልከው ነገር፡ ከአንተ ጋር እሄዳለሁ አለው።” አምንሃለሁ ብሏል፡ ጌታን ተቀብሏል። አሁን ግን ከባዱ ጨለማ ደረሰ፡ በመንገድ ላይ ሳሉ፡ መልዕክተኛ እየሮጠ መጣ። እራሱን አሰወግዷል፡ የኢየሱስ ተከታይ እንደሆነ፡ እራሱን በህዝብ ፊት ገልጧል።

123 አሁን ግን አንድ እየሮጠ መጣና፡ “አሁንስ ማንንም አታድክም፡ ብላቴናይቱ አርፋለች አለው። ትላንትና አረፈች። በቃ ሞታለች። ካሁን በኋላ እራስህን አታሞኝ።”

124 አቤት፡ ትንሿ ልቡ፡ ልታመልጠው ተቃረበች። ነገር ግን ዞር አለና፡ የኢየሱስን አይኖች “አትፍራ አላልኩህምን? አሉት፡ የእግዚአብሄርን ክብር ማየት ከፈለግክ፡ አትፍራ። እሄዳለሁ ብየሃለሁ። ለምን ትፈራለህ? ”

125 አስቀድሞ እመጣለሁ ብሎታል። አስቀድሞ ይሄን አደርጋልሁ ብሏል፡ እነሆም አሁን ያደርጋል። አሜን። በዘመን ፍጻሜ ወደ ወደ ትዕይንት መድረክ እንደሚገለጥና ድሮ እንዳደረገ ትናንት ማታ እንደተነጋገርነው፡ እነኚህ ነገሮችን እንደሚያደርግ ተናግሯል። ይሄው አሁን ያደርጋል። የሚያስፈራችሁ ምንድነው?

126 በመጣ ጊዜ፡ አስታውሱ፣ መጣና ከሙታን መካከል ጠራት። ወደ ትዕይንቱ መድረክ መጣና ከሙታን መካከል ጠራት።

አንድ ጊዜ፡ ዓይነ ሰውሩ በርጤሜዎስ፡ የፈተና ወቅቱ ጠርዝ ነካበትና።

127 የወንጌል ሰራተኞች ማሕበር ግብዣ—በኢያሪኮ ተዘጋጅቶ ስለነበረ፡ ኢየሱስ በቦታው ተግኝቶ ነበር፡ ዘኪዮስን በዚያ ቦታ አገኘው። በጎዳናው ዛፉ ላይ ወጥቶ፡ አግኝቶት ነበርና። እዚያ ሳለ… መቼም፡ እርግጠኛ ነኝ፡ ያዘጋጀው አንዳች ነገር አልነበረውም። እያችሁ? ወደዚያ በወረደ ጊዜ ግን፡ እሱን—አገኘውና፡ ዘኪዮስ ከሱ ጋር ሄደ።

128 ሽማግሌው ዓይነ ሰውር በርጤሜዎስ ከልጅነቱ ጀምሮ ዓይነ ሰውር ነበር። ስለዚህ ኢየሱስ በዚህች በር ሊመጣ ይችላል ብሎ፡ ይጠባበቅ ነበር። አንድ ቀን ግን ብዙ ጩኸት ሰማ፡ እና ሰው ሁሉ በአጠገቡ እያለፈ ነው።

129 አንድ ካህንም እንዲህ ሲል ሰማ፦ “ሄይ! ሄይ፣ አንተ፣ እዚያ ወደ ኮረብታው የምትወጣ ሰው! እ—እ—እ… ሙታንን እንደምታስነሳ ሰምተናል። እዚህ ላይ ሙሉ የመቃብር ሰፍራ አለ። አንተ መሲህ ከሆንክ፡ መሲሁ ከሆንክ፡ ወደዚህ ና ‘ና እነዚህን ሙታን አስነሳ።”

130 ታውቃላችሁ፡ ያ ዲያብሎስ አሁንም አለ፣ በሃይማኖት መልክ፣ እያችሁ፡ በተመሳሳይ መንገድ አለ። እያችሁት?

131 “አንተ መሲህ ከሆንክ፡ ሙታንን ታነሣለህ፡ እኛም… እዚህ ያለው የመቃብር ቦታችን ብዙ ሙታን አሉበት። ና።” አቤት፡ ይህም ያኛውም፡ ሁሉ ይጮሃል፤ ሌላም “ሆሳዕና ለነብዪው!” ይላል። ሌላኛውም **እንዲህ፣ እንዲያ፣** ወይም **ሌላ** ነገር ይናገራል። ድብልቅልቅ ብሏል!

132 ሽማግሌው አይነ ስውሩ፦ “ወይ'ኔ፡ እኔ ወደዚህ ይመጣል ብየ አሰቤ። ወደዚያ ወጣ፣ አመለጠኝ። በማይሆን ቦታ አስቀመጡኝ።” ብሎ አሰበና መጮህ ግዴታ ሆነበት። “እርሱ ቃል ከሆነ፡ እራሱ እግዚአብሔር ነው፡ መሆን አለበት፡” ብሎ አሰቧል። ስለዚህ፣ “የዳዊት ልጅ፡ ኢየሱስ ሆይ፡ ማረኝ!” በዚያ የጭንቅ ሰዓት ውስጥ ጠራ።

133 አሁን ኢየሱስ፣ እዚህ ላይ ማስታወሻ ከያዛችሁ፣ ኢያሪኮ ውስጥ ነው። እንደሚሉት ኢየሱስ ከነበረበት፡ አንድ መቶ ሐምሳ ያርድ ያህል ርቀት ተቀምጦ ነበር ይባላል። በሺዎች የሚቆጥሩ ሰዎች በዙርያው ይዋከባሉ፡ የዚያ ሰው ጩኸት የሚሰማበት መንገድ አልነበረውም። በፍጹም። የሆነ ነገር ግን ተሰማው። እና ቆመ።

134 አንዲት ምሽት ግን፦ “ከዚያም ኢየሱስ ቆመ፡” ብየ መሰበክ እፈልጋለሁ። አቤት! “ከዚያም ኢየሱስ ጐንበስ አለ።” አቤት!

135 ኢየሱስ ሲቆም፡ ምን ሆነ? ጠራው። “አይዞህ። መምህሩ መጥቷል፡” አሉ ደቀ መዛሙርቱም፡ “ይጠራሃል። እየጠራህ ነው አሉት።” ከዚያ ሕዝብ መካከል ጠራው።

አሁንም ተመሳሳይ ነገር ያደርጋል። ገባችሁ ወይ? እያችሁ?

136 “መምህሩ መጥቷል ይጠራሃል።” እና ከመታወር ወደ ብርሃን፡ ከጨለማ ወደ ብርሃን ጠራው። እርሱንም ጠራው፡ ከሞት ወደ ህይወት አመጣው። “መምህሩ መጥቷል ይጠራሃል።” በጠራው ጊዜም፡ ዓይኑን አበራለት።

137 የደም ችግር ያለባት ምስኪኗ ሴት፡ አንድ ጊዜ፡ በኮረብታው ላይ፡ ገንዘቧን በሙሉ፡ ለሐኪሞች እውጥታ ጨርሳ ነበር። እሷ፡ ያለጥርጥር፡ ጥማዶቻቸውን—ሸጠዋቸዋል። እርሻውን—ሸጠውታል፡ በዕዳ ተይዟል። የቻሉትን ሁሉ በሐኪሞቹ ላይ አፍሰሰዋል፡ አንዳቸው ግን አልጠቀሟትም። ሳያቋርጥ እየባሰባት እና እየባሰባት ይሄዳል። ደሙ አያቆምም። ሳያቋርጥ፡ ዝም ብሎ ይፈሳል፡ ውስጥ እየዘለቀ እየዘለቀባት ነው።

138 አንድ ቀን ግን፡ እሷ ከምትኖርበት ተራራ ተቀምጣ፡ ሹራብ እየፈተለች ሳለች፡ ወደ ሸለቆው አማትራ፡ ጀልባ ሲመጣ አየች። ሰው ሁሉ “ሆሳዕና ለነብዪው!” እያለ መሮጥ ጀመረ፡

139 እሷም ስለሱ ሰምታ ነበር። እምነት ከመሰማት ነው። እና እሷም “ወደዚያ እወርዳለሁ እርሱንም አየዋለሁ፡” አለች።

140 ወደዚያ ወርዳ፡ የእግዚአብሄርን ቃል በስጋ ሲገለጥ ለመጀመርያ ጊዜ ባየችው ጊዜ፡ እሱ እንደሆነ የምታውቅበት፡ ከአነጋገሩ እና ከአኳኋኑ አንዳች ነገር ነበረው። አዎን፡ ወዳጄ። “አቤት፡ በሆነ መንገድ እንዲያየኝ ባደረግኩት፡ እንደምንም ብየ ጫፉን መንካት በቻልኩ!” ከዚያ በኋላ በህዝቡ መኃል በስውር ገብታ ልብሱን ነካች።

141 አሁን አስታውሱ፡ እርሱ ሲነካው የተሰማው ጣቶቿ አልነበረም። አይደለም፡ ወዳጄ፡ ምክንያቱ የፍልስጤም ልብስ ጥልጥል ብሎ የሚወርድ ስለሆነ። እሱም... እና እነሱ-...

ጴጥሮስም "ሰው ሁሉ እያጋፋህ ነው፡" ብሎታል።

142 እሱ ግን "ይሄኛው ለየት ያለ እነካክ ነው። ኃይል ከእኔ ወጥቷል ደከምከም አርጎኛል፡" አለ።

143 መጣ ኢየሱስ። ገንዘቧ አልቋል፡ ያላት ሁሉ ጠፍቷል፡ ደሙ መቆም ባልተቻለበት፡ ሐኪሞችም ማስቆም ባልቻሉበት የጨለማው ሰዓት ግን፡ ኢየሱስ መጣ። እና ምን አደረገ? ጠራት። እስኪያገኛት ድረስ ዘወር ብሎ ተመለከተ፡ እርሱም "ደም ይፈስብሽ ነበር፡ አሁን ግን ቆመ፡" አላት።

144 "እርሱ ትናንትናም፣ ዛሬም፣ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።" "መምህሩ መጥቷል ይጠራሻማል። መጥቶ ጠራት።" ወደ ጤናም መለሳት።

145 ትናንት ማታ እንደተነጋገርነው፡ ጉድጓድ አጠገብ የነበረች ምስኪን ሴት ተስፋዋ ሁሉ ጠፍተዋል። ምናልባትም፡ አምስተኛ ባልዋ ትቷት፡ ስድስተኛው የዚያኑ ቀን ማታ ሳትይዘው አትቀርም፡ ሥነ ምግባሯ፡ ተበላሽተዋል። በዚህም—ምክንያት ትንሽ ተጠራጥራዋለች። መጽሐፍ ቅዱስ፡ እንብባለች፡ መልካም እመቤት መሆን እንደምትፈልግ፡ አያጠራጥርም።

146 ወደ ውሃው ስትወርድ፡ አስራ አንድ ሰዓት ገደማ ሆኗል። ቅዱሳን ሴቶች በሚወጡባት ማለዳ መውረድ አትችልም። እነሱ በማለዳ ውሃቸውን እና፡ እንሥራዎቻቸውን፡ በራሶቻቸው ላይ ተሸክመው፡ ይመለሳሉ። እሷ ግን አብራቸው ለመሄድ፡ ከእነርሱ ጋር መሆን አትችልም። በዚያ ዘመን፡ ትክክል እና ስሕተት አንድ ላይ ስለማይስማሙ፡ በመካከላቸው መለያየት ነበር። ሥነ ምግባር የጎደላቸው ሰዎች ለብቻቸው ስለሚሆኑ፡ ከሌሎቹ ጋር መውረድ አልተቻላትም። እንድትቀላቀላቸው አይፈልጉም። በዚህም ምክንያት ሌሎች ሁሉ ወርደው ውሃቸውን ቀድተው ከተመለሱ በኋላ... እሷ ደግሞ በተራዋ መጣች።

147 እና እንሥራዋን ራሷ ላይ አድርጋ መጣች፡ በመንገድ ላይ፡ እያሰበች እንደነበረች አያጠራጥርም፡ "ይህ አሁን፡ ያገባሁት ሰው፡ ወይም፡ ለአንድ ሌሊት አብሮኝ የሚያድረው ሰው፡ አጠራጥሮኛል። ቀልዳ ቀልድ፡ የሚያበዛ ሰው ነው። እኔ—ስለ'ሱ የማውቀው ነገር የለኝም። ከማሕበረሰብ የተገለልኩ ሰው ነኝ። ዕድልም አላገኘሁም። ወደ እነዚህ ቸርቾች መግባት አልችልም፡ ዝም ብየ እመለከታቸዋለሁ... እንጂ እነሱ! ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም። ጨንቆኛል። መጽሀፍ ቅዱሱን ሳነበው ግን፡ በእውነት፡ አንድ ቀን፡ ነብዩው ወደዚህ ትዕዪንት መድረክ ይመጣል። በርግጥ እነሱ እንዲህ አይነት ነገር የለም ብለዋል፡ እንዲሁም ደግሞ፡ 'ምናልባትም ብዙ መቶ አመታት፡ እና ብዙ ሺ ዓመታት አልፈዋል። ለብዙ ሺ ዓመታት ይሄን ስንጠባበቅ ኖረናል፡ እስከ አሁን ድረስ አንዳች ነገር የለም፡ አሁንም አንጠብቅም።' ሁሉም እንዲህ ነው፡ 'ኦህ፡ አንፈልግም፡ ቸርቾች እና ሌላ ነገሮች፡ አሉን። አሁን እንዲህ ያለ ነገር አያስፈልገንም ብለዋል።'" ከዚያም፡ እያሰበች ወደዚያ ትሄድ ነበር።

148 ታውቃላችሁ፡ ስለ'ሱ ስታስቡ፡ ያኔ ይገለጥላችኋል። ልክ ትናንት ማታ እንደተማርነው፡ እንደ ኤማሁስ መንገደኞች ነው።

149 እና እሷ እነዚህን ነገሮች እያሰበች ሳለች፡ አንድ ሰው "ውሃ አጠጪኝ፡" ሲላት ሰማች።

150 ጭልም ባለባት፡ ወኔዋ በከዳት ሰዓታት ውስጥ። ምነው ምን መጣባት? ምናልባት አንዲት ቆንጆ ኮረዳ፡ ይሄን ዓይነት ኑሮ ለመኖር ተገዳ ይሆናል። አንዳንዴ በዚህ አይነት አወጣጥ ሲወጡ፡ የልጆቹ ጥፋት ሳይሆን፡ የወላጆቿ ጥፋት ነው። እና ይህችም ምናልባት በዚያ በነበረች ጊዜ፡ፍሪዙ ጸጉሯ ወደታች ተለቆ፡ ስትሄድ፡ ተሰላችታለች፡ ደክሟታል፡ ከጎኗ ማንም የላትም፡ ምናልባት የልጅ ጉዳይ፡ ከበስተጀርባ ሌላ ታሪክ ይኖራታል።

151 ብቻ፡ አንድ ነገር አውቃለሁ፡ መጽሀፍ ቅዱስን አንብባለች፡ መጽሐፍ ቅዱስን አምናለች። በልቧም፡ እንዲህ ብሎ የሚናገር ዘር ተዘርቶባታል፡ "ይህ ነገር ሲፈጸም፡ ማወቄ አይቀርም አለች።" ለዚህም ተመድባ ነበርና።

152 ይሁዳ አብሮት ሆኖ ያደረገውን ተመልከቱት። ውስጠኛውና ታችኛው የልቡ ስፍራ ጥቁር ነበር። በሚሰራው ስራ ላይ ብርሃኑ ሲያንጸባርቅበት ነበር፡ ይሁን እንጂ በልቡ አያምንም ነበር። እቺ ደግሞ ህይወቷ ጨልሟል… እያችሁ፡ ብርሃን አልበራላትም ነበር። ይሁን እንጂ፡ ስታምነው ተመልከቷት፡ አመነች፡ ህይወቷ ግን ሌላ ነው፡ ብርሃን በበራባት ጊዜ፡ ጨለማውን ገፈፈው። እሱኛው ብርሃን በበራበት ጊዜ ግን፡ ጭራሽኑ አጨለመው። ልዩነቱ ይህ ነው።

153 እያችሁ፡ ለዚያች ዓላማ ተወልዳ ነበር። እንዲህ—አለች፡ ሰንት ባሎች እንደነበሯት፡ ሲነግራት… ምን ሆነ? ወድያው ግራ ተጋባች። ጭንቀት ውስጥ ገባች። እንዲህ አለች፡ "ጌታ ሆይ፡ አንተ ነቢይ እንደሆንህ አይሃለሁ። መሲሑ ሲመጣ እነዚህን ነገሮች እንደሚያደርግ አውቃለሁ።"

154 ወድያውም ጠራት። ወድያውኑ ጠራት። "ከአንቺ ጋር የምነጋገረው እኔ፡ እርሱ ነኝ።" በእግዚአብሄር ቃል አወቀችው። እሱም ከሐጥያት፡ ወደ ህይወት ጠራት። ስሟም በመጽሀፍ ቅዱስ ሰፍሯል፡ ስለዚህ ዛሬ ዘለአለማዊ ህይወት አግኝታለች።

155 ለእናንተም እንዲሁ ሊጠራችሁ ይቻለዋል፡ ምክንያቱ ትላንትናና፣ ዛሬ፣ እስከ ዘላለም ድረስ ያው ነው። ጉዳይዋ…

156 አዎን፡ ሰነ ምግባሯ ሁሉ ብልሹ ነበረች፡ ይሁን እንጂ ልብን የማንበብ አቅም እንደነበረው አወቀችው። መሲሕ መሆን እንዳለበት ተረድታለች። ከዚያ በኋላ ኢየሱስ ራሱ፡ "እኔ እሱ ነኝ፣ እኔ እሱ ነኝ፣" ባላት ጊዜ እሱ እንደሆነ አውቃለች።

157 አንድ ጊዜ ደቀ መዛሙርት ሁሉ በጀልባ ውስጥ ነበሩ፡ ተስፋቸው ሁሉ ጠፍቷል። ሲሄዱም ኢየሱስ ከእነሱ ጋር አልነበረም፡ ማዕበሉም፡ ልክ በአልዓዛር ቤት—እንደነበረ ማዕበል ነበር። ተሰፋ ሁሉ ጠፋ። ትንሿ ጀልባ በውኃ ተጥለቅልቃለች። እየጮሁ እያለቀሱ ነበሩ፡ ምናልባትም እየጸለዩ ነበር፡ መብረቁም ይብረቀረቃል፡ ታንኳይቱም በውኃ ተሞልታለች፡ ቋሚው መቅዘፍያ ወድቋል፡ የእንጨት መቅዘፍያውም ተሰብሯል፡ እያለቀሱ፡ አንዱ ሌላኛውን አጥብቆ ይዟል።

158 እጅግ ጨለማ በሆነባቸው ሰዓት ላይ፡ ኢየሱስ እየተራመደ ቀረባቸው። ምትሃት ሆኖም ታያቸው። እንደ መናፍስት፡ አስፈሪ መሰላቸው፡ በፍርሃትም ጮኹ።

159 ዛሬም ያው ነው። ኢየሱስ እጅግ በጨለመባችሁ ጊዜ ይመጣላችኋል፡ እናንተ ግን ትፈሩታላችሁ። ማን እንደሆነም አታውቁም።

160 እነሱ ማን እንደሆነ አላወቁትም። ተንጫጩ፡ “ወይ’ኔ፡ ምትሃት ነው!” ተባባሉ።

161 ወድያው ግን ጠራቸው፡ “አትፍሩ፡ እኔው ነኝ፡” አላቸው። እጅግ በጨለመባቸው ጊዜ፡ ረዲኤታቸው፡ ኢየሱስ መጣ። የሱ አመጣጥ ሁሌ እንዲህ ነው፡ እጅግ በጨለመች ሰዓት ላይ ይገለጣል። ኢየሱስም መጣ እራሱንም ገለጠላቸው፡ ቀረባቸውም።

ጴጥሮስም ቀበል አረገና “አንተ ከሆንክ፡ በውኃው ላይ እንድራመድ እዘዘኝ፡” አለው።

ኢየሱስም “ና፡” አለው።

162 ወዳጆች ሆይ፡ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? በዚህ ዘመን ለሚኖሩም በቅርብ ጊዜ ይመጣላቸዋል። አሁን፡ በዚህ በጨለማው ጊዜ ቤተክርስትያን ያለችበት ሁኔታ አያስደነግጥም ወይ?

163 እዚህ ጋር አንዳች ነገር እናገራለሁ። ዶክትሪን አይደለም። ትንቢት እናገራለሁ። የተፈጸመው ነገር አውቃችኋል? በቅርብ ጊዜ፡ እንዲህ ይሆናል፡ ቃሌን አሰምሩበት፡ እያንዳንዳቸው የሐይማኖት ተቋማት ኢኩሜኒካል ካውንሰል ጋር ይቀላቀላሉ። ካልሆነ ግን፡ ከካውንሰሉ የሚሰጡ ድጋፎችን ማግኘት አይችሉም። ስለዚህ፡ ቅጣት ይኖራል፡ ማንም ሰው ወደነዚህ አብያተ ክርስትያናት፡ ወይም ወደ ቤተክርስትያን መሄድ አይችልም፡ ከቸርቻችሁ ምልክቱ ካልተቀበላችሁ በስተቀር፡ መግዛትም መሸጥም አትችሉም። እያችሁ አሁንም ዳግም፡ እንደ ድሮው፡ ለአውሬው ምልክቱ ይሆናል። ቸርችም፡ መንፈሳዊ የሆኑ ሰዎችም፡ ይሄን ማስተዋል ጀምሯል።

164 እንደው፡ እናንተ ጴንጤቆስጤዎችም፡ አውቃችሁታል። አሁን ይሰማችሁ ጀምሯል። አብዛኞቹ የጴንጤቆስጤ ድርጅቶች፡ ቸርቻቻችሁ ሁሉ፡ ስም መጥራት ባያስፈልገኝም፡ እነዚህ ሁሉ ግን—እየተቀላቀሉ እንዳሉ እናንተም ታውቃላችሁ። እነሱ እራሳቸው ነን ብሏል። እንደዛ ሰትሆኑስ፡ ማድረግ የሚጠበቅባችሁ ነገር ምንድርነው? ኢቫንጀሊካዊ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ትምህርታችሁን ትክዱታላችሁ። የመጽሐፍ ቅዱስ ዶክትሪናችሁን ትክዳላችሁ።

165 ከዚያ በኋላ ምዕመናን ሁሉ ይሄን መቋቋም ይሳናቸዋል። ዳግም-የተወለዱት እውነተኛ ክርስትያኖች አስቀድመው ይሞታሉ። ቃል አስጠንቅቋቸዋል። ይሄ እንደሚመጣ ያውቃሉ። አዎን፡ ጌታየ።

166 አይገርምም ወይ? እጅግ በጨለሙብን ሰዓት ላይ፡ ኢየሱስ መጣና ጠርቶ፡ “አትፍሩ፡ እኔ ነኝ። አለን። አሁንም እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ። ቃሌን ለእንናተ ልገልጽ መጥቻለሁ።” ያኔ እንደነበረ፡ አሁንም እሱ ያው ነው። እኔ ይሄን አደርጋለሁ ብሎ ነበር። ኦ፡ ማይ! መምህሩ መጥቶ ጠራን።

167 እዚህ ከተቀመጡ ሰዎች መካከል፡ ብዙ የታመሙ፡ እዚህ እንዳሉ አያጠራጥርም፡ ዶክተር ተሰፋ እንደሌላችሁ—ነግሯችኋል። ምናልባት እጅግ

በጨለመች ሰዓት ትገኙ ይሆናል፡ ነገር ግን፡ አስታውሱ፡ መምህሩ መጥቶ ጠርቷችኋል።

168 አንድ ቀንም፡ መምህሩ አንድ ቀን ይመጣል፡ ስሞቻቸው በበጉ የህይወት መጽሐፍ የተጻፉትን ሁሉ ይጠራቸዋል። ስማችሁ ከሌለ፡ አሁን እንዲኖር አድርጉ፡ እሱ ይመጣል ሁሉንም ይጠራል። በመቃብር ያሉት ሳይቀሩ ድምጹን ሰምተው ህያዋን ይሆናሉ። መምህሩ ይመጣል ይጠራችሁማል። አሁን እሱ እየጠራ ባለበት ጊዜ፡ ምክሬ ለእናንተ፡ አቤት እንድትሉ እና ለዚያ ቀን እንድትዘጋጁ ነው።

169 እመጣለሁ ብሏል፡ የዚህ ዘመን ተስፋ ቃልም ይህ ነው። ያኔ የሰራቸው ነገሮች፡ አሁንም በድጋሚ ያደርጋቸዋል፡ አሁን ደግሞ መምህሩ መጥቷል ይጠራችሁማል።

170 ራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ። ስድስት ሉክ ያህል ቀርቶኛል፡ ይሁን እንጂ—አሁን አልጨርሰውም። ቶሎ እለቃችኋለሁ ብየ ቃል ገብቻለሁ፡ አሁን ከሩብ ሆኗል። ራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ።

171 የሰማይ አባት፡ ጌታ ሆይ፡ አሁንም እንደገና ይፈጸም። “ኢየሱስ መጥቷል ይጠራችሁማል፡” ብየ የተናገርኳቸውን ሁሉ። ሲመጣ ምን ያደርጋል? ይጣራል። ጌታ ሆይ፡ አሁንም ይፈጸም። ዛሬ ማታ ጌታ ኢየሱስ—በመንፈስ መልክ፡መንፈስ ቅዱስህ ሆኖ በህዝቡ መካከል ይምጣ። ዛሬ ይምጣና እራሱን ያሳይ፡ እራሱንም ይግለጥ። እንደ እነዚያ ሰዎች፡ እነሱ እንዳመኑ፡ ጌታ ሆይ፡ እኛም ድግሞ፡ እንመን። ዛሬ እዚህ፡ ምናልባት ይሄን እድል አግኝተው የማያውቁ፡ ብዙዎች አሉ። ለእነሱም ይሄን ታደርግላቸው ዘንድ ጸለይን። ስለ እግዚአብሄር ክብር፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ጸለይን። አሜን።

172 አዎን፡ እህቴ፡ አንቺ ግን ቀጥይበት። በጣም ጥሩ ነው። ወደፊት ቀጥዪ። ኑ፡ ሰው ሁሉ፡ በዝምታ ይቆይ።

173 እሱ መምጣቱ አምናችኋል? መጥቷል። እሱ ሲመጣ አሁንም ይጣራል? አሁን እናንተ ካመናችሁ ብቻ ነው። የእግዚአብሄርን ቃል ብቻ እመኑ እንጂ፡ እግዚአብሔር ያደርግላችኋል።

174 አሁን ተመልከቱ፣ የጸሎት መስመር ለመጥራት ጊዜ የለኝም። ጌታ ቢፈቅድ፡ ዛሬ ማታ፡ እዚያ እጠራችኋለሁ። መምህሩ መጥቷል። በመጨረሻው ቀን ቃሉን ሊፈጽም መጥቷል። እሱ ያኔ የነበረው ሁሉ፡ ዛሬም ያው ነው። ዛሬም እሱ የእግዚአብሄር ቃል ስለሆነ፡ ያኔ የነበረው መገለጫዎቹ እና መታወቂያው፡ ዛሬም ያው ነው። ታምናላችሁ? [ጉባኤው “አሜን፡” አለ።—አርታዒ] የእግዚአብሄር ቃልም የልብን ሰሜት፣ እና ሐሳብ መርማሪ ነው። ስለዚህ ያኔ ያደረገው፡ ሁሌም የሚሰራበት መንገድ ነው። አሁንም ያው ነው። ያንኑ ነገር አሁን ቢያደርግስ፡ ታምኑታላችሁን? እንድታምኑት ያደርጋችኋልን?

175 እዚያ ያላችሁ ሰዎች ሁላችሁ፡ አስቀድሜ ግን፡ ከተቀመጡ ሰዎች መካከል፡ ምናልባት እኔ የማውቀው፡ የማውቀው ካለ ልመልከት።

176 ከእናንተ መካከል፡ **እዚህ** ካላችሁ፡ እኔን የማታውቁኝ፡ እጆቻችሁን አንሱ፡ እኔ ስለ እናንተ አንዳች እንደማላውቅ የምታውቁ፡ ደግሞም የታመማችሁ፡

እጆቻችሁን አንሱ። ሁሉም፡ ይመስለኛል። እሺ፡ አሁን፡ እመኑ። በሙሉ ልባችሁ እመኑ። እንዳትጠራጠሩ። እምነት ይኑራችሁ። እግዚአብሄርን እመኑት።

177 በእርጋታ እንድትቀመጡ፡ አሁን ሁላችሁንም እማጸናለሁ። አትተረማመሱ አሁን፡ እባካችሁ። አያችሁ? አያችሁ? እናንተ—ነፍስ፣ ስጋ፣ እና መንፈስ ናችሁ። መንፈሳችሁ… መንፈስ ቅዱስም ቶሎ ይበረግጋል።

178 ስለ መንፈስ ቅዱስ፡ ከብዙ ዓመታት በፊት፡ እዚህ መጥቼ የነገርኳችሁ፡ ሰንቶቻችሁ ታስታውሳላችሁ? የሰዎችን እጆቻቸውን ሰይዛቸው፡ ይህ የመለየት ጸጋ እንደሚመጣ፡ ወዘተ፡ እንደነገረኝ? ታስታውሳላችሁ፡ አስታወሳችሁ? እሱ ግን "ሰዎችን እንዲያምኑህ ካደረግካቸው፡" አለኝ። ከብዙ ዓመታት በፊት፡ አስታወሳችኋቸው እነዚያን ቀናት? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—እርታዒ] ማመን አለባችሁ።

179 ባለፈው እዚህ ጉባኤ ላይ ይመስለኛል፡ አንድ ሰው አየሁ፡ እዚያ ጋር ተቀምጦ ነበር። መንፈስ ቅዱስም… እየሰበኩ እያየሁት ነበር። ሽባ የሆነ ሰው ነው። ክራንች ይዞ ነበር። መጥራት እንደጀመርኩ፡ የሰይጣን ጥቁር ጥላ፡ ወደ ሰውየው መጣ። በአይኖቼ አይቼዋለሁ። ተነስቶ ወጣ። አያችሁ፡ ይህ ሰው ሁሌ ሽባ ሆኖ ይኖራል። እሱ፡ እንደው፡ በሚፈወሰበት በቦታው ቢሆን—ኖሮ… አያችሁ? በቃ፡ ለምን እንደሆነ ግን፡ አላወቅኩም። እንደሚመሰለኝ የጠላት ድምጽ ሰማ። እነዚያን ጥላዎች በመቃወም መቆም ከቻላችሁ፡ እነዚያን ነገሮች ቅርጾች፡ ሁኔታዎቻቸውን፡ እንዴት እንደሚሰሩ ንቁባቸው። አያችሁ፡ እንዲህ…

180 አሁን፡ እኔ መፈወስ አልችልም። እሱ ሊፈውሰህ ይችላል ብሎ የነገረህ ሰው፡ ተሳስተዋል። አሰቀድማችሁ ተፈውሳችኋል። ነገር ግን፡ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መገኘት እውቅናን ስለ መስጠት ነው። ማርታ እሱን ዳግም ማየት ከቻለች፡ የምትሻውን እንደምታገኝ ካወቀች፡ እሱ የተገለጠ ቃል ስለሆነ፣ እኛስ ዛሬ ምሽት ይሄን ለማመን፡ የሷን ያክል ማመን ያቅተናልን? አዎን፡ ማመን አለብን። መጥቷል። እሱ መጥቷል፡ በመንፈስ ቅዱስ አምሳል መጥቷል። ማንነቱ እሱ ነው። አሁን ጸልዩ።

181 እዚህ ጋር፡ አያችሁት፡ እዚህ በእኔ አጠገብ፡ አብሮኝ የቆመ፡ ሰው ቢኖር ኖሮ፡ ብቻ—ጸልዩ ብቻ፡ አያችሁ፡ በህንጻው ዙርያ ሁሉ፡ ብዙ ሰው እየጸለየ ነው። ማየት ብቻ ነው ያለባችሁ። "ወንድም ብራንሃም፡ ማለት… " አትችሉም፡ አይቻልም፡ ወዳጄ። እኔ—እኔም፡ ለእኔ ከምታዩት ህልም በላይ አልችለውም። አያችሁ? ህልም ልታልሙ ትችላላችሁ። እግዚአብሄር፡ ስለ'ኔ ህልምን ሊያሳያችሁ ይችላል፡ ታምኑታላችሁ፡ ይሁን እንጂ በራሳችህ ልታዩት አትችሉም። "ወንድም ብራንሃም፡ እኔ አሁን ለአንተ ህልም አልምልሃለሁ፡" ልትሉኝ፡ አትችሉም። አይሆንም፡ ይሄን ማድረግ አትችሉም። እኔም ራዕይን ማየት አልችልም። ያ ለእናንተ ህልም እንድታዩ የሚያደርጋችሁ፡ እሱ እራሱ ነው የሚያደርገው። ራዕይ በተመለከትም እንዲሁ ተመሳሳይ ነው።

182 በዚህኛው መስመር መጨረሻው ላይ፡ አርቲራይትስ ያለበት ሰው አያለሁ። በሙሉ ልቡ ማመን ከቻለ፡ እግዚአብሄር ከአርቲራይትስ ይፈውሰዋል። እንደሚፈውሶት ያምናሉ፡ ጋሼ? እዚያ ጋር የተቀመጥከው፡ ሜክሲካዊ ሰው፡ በረድፉ በስተመጨረሻ ያለኸው፡ ታምነዋለህን? በጣም ጥሩ፡ ጋሼ።

183 ከአንተ ቀጥላ ያለች ሴት፡ እሷም፡ አርቲራይትስ አለባት። እግዚአብሄር እንደሚፈውስሽ ታምኛለሽ፡ እመቤት? (**ይሄ** ነገር የገደል ማሚት ይኖረው ይሆን'ዴ? ሰዎች የሰሙኝ አልመሰለኝም።) ታምኛለሽ? በጣም ጥሩ።

184 ከጎኗ ያለችው ሜክሲካዊት ሴትስ? በሆድ ህመም እየተሰቃየች ትገኛለች። እግዚአብሄር ሆድሽን እንደሚፈውስሽ ታምኚአለሽ፡ እመቤት?

185 አገኛታዋለች። ብርሃን ሲወርድ ሳይ ያ ማለት ሆነ ማለት ነው። አዎ። ይሀው ነው። ነክቷታል። እዚያው ዙሪያዋን እየተሽከረከረ ነበር... [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።]... ያንን ያደርጋል። አያችሁ? እምነት ሲያገኝ ያረጋል! አያችሁ፡ "በአለማመናቸው ምክንያት ብዙም ነገር አላደረገም።"

186 እዚህጋ ተቀምጣ የምትጸልይ ሴት አለች፡ እዚህ ጋር። ፈርታለች። መፍራትም አለባት። በካንሰር ደረጃ የደረሰ ነገር አለባት፡ በጣም አስከፊ ነው። እኔ አንቺን አላውቅሽም፡ እግዚአብሄር ግን ያውቅሻል። እግዚአብሄር ስለዚህ ካንሰር፡ ወይም ሌላ ነገር ሊነግረኝ እንደሚችል ታምኛለሽ? እኔን እዩኝ። አየሽ፡ ብዙዎች የሚጸልዩ ስላሉ፡ ለዚህ ነው ይሄን ያልኩሽ። ወደኛ ተመከቺ። አሁን፣ አዎን፣ አንቺ ከዚህ አይደለሽም፣ መኖርያሽ እዚህ አይደለም። አንቺ ፖርተርቪል፣ ካሊፎርኒያ ከሚባል ቦታ ነሽ። ትክክል። እሱ እንደሚያውቅሽ። እግዚአብሄር ማን እንደሆንሽ ሊነግረኝ እንደሚችል ታምኛለሽ? ስምሽ ወይዘሮ ዊንትሃም ትባያለሽ። ትክክል። አሁን እመኚ፡ ካንሠሩ ለቆሽ ይሄዳል። "ካመንሽ።" እግዚአብሄር ከአንቺ የሚጠብቀው ይህ ብቻ ነው። "ካመንሽ።"

187 በሙሉ ልብሽ ማመን አትችይም ወይ? እስኪ **በዚህ** መደዳ ላይ፡ አንድ ሰው ማመን አይችልም ወይ? መምህሩ መጥቷል ይጠራቿል። ከሞት ወደ ሕይወት፣ ከበሽታ ወደ ጤና ይጠራቿል።

188 ራሱን ዝቅ አድርጎ፡ የሚጸልይ፡ አንድ ሰው እዚህ ከኋላ አለ። የሚጸልየው ስለራሱ አይደለም፡ የሚጸልየው ስለሌላ ሰው ነው። ስለ—ሴት ነው። ልጁ ናት። ታምናለህ፡ ጋሼ? አንተም እግሮችህ ላይ ችግር አለብህ። የጉልበት ላይ ችግር አለብህ። ትክክል። እርሱ ከአንተ ጋር ነውና፡ ማልቀስ አያስፈልግም። ልጅህ በሆስፒታል ውስጥ ናት፡ አይደለችም እንዴ? ትዩበርክሎሲስ ነው። እመን። ታምናለህ? መምህሩ መጥቷል እሷን ጠርቷታል። እንደ አባቷ፡ አንተ ታምናለህ ወይ? እሺ ትላለህ? ዛሬ ይድረስላት፡ ለአንተም ይሁን። ማብቂያው ይሁን።

189 እዚህ አንድ ትንሽ ልጅ፣ ትንሽ ፊት ቡናማ-ቀለም ያለው ልጅ አለ። በቆዳ በሽታ፡ እና በአስም እየተሰቃየ ነው፡ትንሽ ሜክሲካዊ ልጅ፡ ሜክሲካዊ ልጅ እዚያ ተቀምጧል። የዚህ አካባቢ ተወላጅ አይደለም። ከሳን ሆሴ ነው። ታምናለህ፡ ልጄ? ሌላ ነገር፣ አባትህ እዚህ ካንተ ጋር ነው። አገልጋይ ነው። ትክክል። ጊታ ስምህ ማን እንደሆነ ሊነግረኝ እንደሚችል ታምናለህ? እጅግ በብርቱ እንድታምን ያደርግሃልን? ስምህ ሩበን ነው። አሁን እመን። አህ-ሀም። እግዚአብሔር ይፈውስሃል።

190 መምህሩ መጥቷል ይጠራህማል። ሀጢያተኛ፡ ሆይ፡ በሽተኛም፡ ሆይ፡ መምህሩ በሰው ልጆች ላይ፡ በአማኞች መካከል ሲገለጥ አይታይህምን? አማኝ ልጆቹ ወደ ጤና ሊመልስ መጥቷል። ሐጥያተኛውን ወደ ንስሐ

ሊመልስ መጥቷል። ባክ አድራጊዎች፡ የቸርች አባላት፡ መምህሩ መጥቷል ይጠራችሁማል።

191 ታምናላችሁ? አሁንስ ስለ ልመናችሁ ታምናላችሁ ወይ? ካመናችሁ፡ እጆቻችሁን ከፍ አድርጉና፡ "ስለ ልመናዬ እምናለሁ፡" በሉ። ተንስታችሁ በእግራችሁ ቁሙና አሁን ተቀበሉት። መምህሩ መጥቶ ይጠራችኋል። ማንም ሁን፡ ምንም አይነት ልመና ይኑርህ፡ መምህሩ መጥቷል ይጠራህማል። ትላንትናና፣ ዛሬ፣ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው ነው።

192 ታናሿ ሴት ወደ ከተማ ገብታ፡ "ኑና፡ ችግሬን ሁሉ የነገረኝን ሰው ተመልከቱ፡" አለች። እናንተ ወደ ከተማ አልሄዳችሁም። መጥታችሁ ግን፡ እራሳችሁ አይታችኋል፡ ስለዚ መምህሩ መጥቷል ይጠራችሁማል።

193 እጆቻችሁ ከፍ አርጉ እና አመስግኑት፡ "ጌታ ኢየሱስ፡ ሐጥያተኛ ነኝና፡ ይቅር በለኝ፡ በሉት። ባክ አድራጊ ነኝና፡ ጌታ ሆይ፡ መልሰኝ። መንፈስ ቅዱስ ያስፈልገኛል፡ ሙላኝ። ታምሜያለሁ፡ ፈውሰኝ። ሰላላ ነኝ፡ አበርታኝ።" መምህሩ መጥቷል ይጠራችሁማል። አሁን እጆቻሁን አንሱና አመስግኑት። አሜን።

194 ("አመሰግነዋለሁ፣ አመሰግነዋለሁ፡" የምትለዋን ትንሿ ኮርድ አርግልን። **አመሰግነዋለሁ**። ታውቁታላችሁ? ዝማሬውን ታውቃላችሁ፣ አይደለም'ዴ?)

ታምናላችሁ?

አመሰግነዋለሁ፡ አመሰግነዋለሁ፡
አቤት፡ ስለ ኃጢአተኞች የታረደውን በግ አመስግኑ፡
ሰዎች ሆይ፡ ሁላችሁ ክብር ሰጡት፡
ደሙ ዝገትን ሁሉ አስወግዷልና።

195 ትወዱታላችሁ? ታዲያ እሱ እዚህ እያለ ለሱ መዘመር አትፈልጉምን? እሱ መንፈስ ነው በህንጻው ዙርያና ውስጥ እየተመላለሰ ነው። ልቦቻችሁን ያውቃል፡ ስለእናንተ ሁሉ ነገር ያውቃል። እስኪ በሙሉ ልባችን፡ ለእሱ እንዘምር።

አመሰግነዋለሁ፣ (ስታመሰግኑት እጆቻችሁን አንሡ)፣
እኔ... (አሁን እሱን አመስግኑት)... አመስግኑት፣
አቤት፡ ስለ ኃጢአተኞች የታረደውን በግ አመስግኑ፡
አቤት፡ ሰዎች ሆይ፡ ሁላችሁ ክብር ሰጡት፡
ደሙ ዝገትን ሁሉ አስወግዷልና።

196 እመቤት፡ ሆይ፡ አንቺ በዊልቸር ያለሽው፡ ባለሽበት ትንሽ እምነት መጨመር በቻልሽ ኖሮ። "እ... " አንድ ጊዜ እንደገና እንሞክር። የሆነ ነገር እየተጠባበቅኩ ነው።

አመሰግነዋለሁ፡ አመሰግነዋለሁ፡
አቤት፡ ስለ ኃጢአተኞች የታረደውን በግ አመስግኑ፡
ሰዎች ሆይ፡ ሁላችሁ ክብር ሰጡት፡
ደሙ ዝገትን ሁሉ አስወግዷልና።

197 አሁን ያንን እየዘመርን ሳለን፡ እየዞራችሁ፡ እየዘመርን፡ የሌላን ሰው እጅ ያዙ፡ "አመሰግነዋለሁ፡" ዘምሩ። አይዟችሁ አሁን፡ በአንድነት።

አመሰግነዋለሁ፡ አመሰግነዋለሁ፡
ስለ ኃጢአተኞች የታረደውን በግ አመሰግኑ፡
ሰዎች ሆይ፡ ሁላችሁ ክብር ስጡት፡
ደሙ ዝገትን ሁሉ አስወግዷልና።

198 ኃጢአተኛው ወዳጄ፡ ሆይ፡ አሁን ወደ ፊት አትወጣምን? ሰዎች ሁላችሁ፡ ወደዚህ መጥታችሁ ክብር ስጡት። እሱን እንደ ግል አዳኝ መቀበል የምትፈልጉ ሰዎች ሁላችሁ። በእርሱ ፊት ቅዱሳን በመንፈስ እያመለኩ ሳሉ እናንተ እዚህ መጥታችህ መቆም አትችሉምን? እንዲህ በሉ፦ “ዛሬ ቃሌን መስጠት፡ እፈልጋለሁ። ላመሰግነው እወዳለሁ። እኔ በእርሱ አላፍርም። እመጣለሁ። አሁን እዚህ፡ እያለ፡ እሱን እንደግል አዳኜ አድርጌ መቀበሌ ዓለም እንዲያውቅልን እፈልጋለሁ።” እኛ እየዘመርን እናንተ አሁን ኑ።

አመሰግነዋለሁ፡ (አትመጡም ወይ? ) አመሰግነዋለሁ፡
አቤት፡ ስለ ኃጢአተኞች የታረደውን በግ አመሰግኑ፡
አቤት፡ ሰዎች ሆይ፡ ሁላችሁ ክብር ስጡት፡
ደሙ ዝገትን ሁሉ አስወግዷልና።

199 እመቤት፡ ሆይ፡ እንዲህ ነው፡ ነይ ወደዚህ። ሌላ በክርስቶስ ህልውና ፊት፡ የሚመጣ ሰው አለ? ወደዚህ ነይ፡ እህት፡ እዚህ ጋር ቁሚ።

200 አሁንስ፡ አዳኙ እንዲሆንለት የሚፈልግ፡ ሌላ ሰው፡ የሚያሳፍር ነገር የለውም። እርሱም እንዲህ ብሏል፦ “በሰው ፊት የሚያፍርብኝ፡ እኔም ደግሞ በአባቴ እና በቅዱሳን መላዕክቱ ፊት እፍርበታለሁ።” አሁን እሱ እዚህ ባለበት ሰዓት፡ በእሱ ካላፈራችሁበት፡ አዳኝ እንዲሆናችሁ ከመረጣችሁት! እናንተ አይታችሁታል። በጣም ፍጹም ነው፡ ቃሉ ራሱ እንዲታወቅ አድርጎታል። አሁን ቅዱሳን እያመለኩ እናንተ ኑ። ወዲህ ትመጣላችሁ?

201 ጌታ ይባርክሽ፡ እናት። የእድሜ ባለጸጋ የሆነች፡ አሮጊት እመቤት እየመጣች ናት። አሁንስ ወዲህ ትመጣላችሁን?

አመሰግናለ... (አሁን ዘምሩት)... አመሰግነዋለሁ...

202 በጣም ጥሩ፡ ወጣት ወዳጆቼ፡ ኑ ወደዚህ ቅረቡ። አመሰግኑት ብቻ። ጌታ ይባርክሽ፡ እመቤት፡ እንደዚህ ነው የሚደረገው። ጌታ ይባርካችሁ፡ እናንተ ወጣቶች።

... ስለ ኃጢአተኞች የታረደውን፡
ሰዎች ሆይ፡ ሁላችሁ ክብር ስጡት፡
ደሙ ዝገትን ሁሉ አስወግዷልና።

203 አገልጋዮቼ ወደ ወጡት ሰዎች እየቀረቡ ሳሉ ሌሎች የሚወጡ ሰዎች ካሉ? ባክ አድራጊዎች ሆይ፡ መጥታችሁ፡ “በህይወቴ አፍሬአለሁ፡” አትሉምን? እሱ እዚህ አለ። የእግዚአብሄር አገልጋይ እንደሆንኩ ታምናላችሁ ወይ? እጆቻችሁን አንሱ። ለምን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በመካከላችን ስላለ። ትመጣላችሁ?

ክብር ስጡት... (መጥታችሁ፡ ክብር ትሰጡታላችሁን? )...
ሰዎች
ደሙ ዝገትን ሁሉ አስወግዷልና...

204 ማርታ፡ ትመጫለሽ፡ ወይስ ከማርያም ጋር በቤት ውስጥ ትቆያለሽ? ወይስ በሆነ ድርጅት ውስጥ እየቆያችሁ፡ እንዲህ ትላላችሁ፦ "ኦ፡ የኔ ቤተክርስትያን በዚህ መልኩ አታምንም፡" ክርስቶስ ሲገለጥ? ወደ ህኳላችሁ ትመለሳላችሁ፡ ወይስ ትመጣላችሁ? "መልካም፡ እኔ ልንገራችሁ፡ እኔ... " በፍጹም። ጊዜው አሁን ነው። እንደ ኢያኢሮስ ሴት ልጅ፡ ሞት በዙርያችሁ ነው።

205 አሁን ኑ! ባክ አድራጊዎች፡ አሁን ኑ። እናንተ ኃጢአተኞች፡ አሁን ኑ። ጊዜው አህን ነው። መምህሩ መጥቷል ይጠራችሁማል። እየጠራችሁ ነው። "እንዴት አውቃለሁ፡" ብላችኋል? የእኔ ድምጽ እየተጠቀመ ነው። ስለበሽታ፣ ስለ ደዌ ለመናገር ድምጼን መጠቀም ከቻለ፡ ኃጢአትን መጥራት እንደሚጠራ አታውቁምን? ኑ ውጡ! አሁን ኑ፡ ይህ የመጨረሻ ዕድላችሁ ሊሆን ይችላል።

206 አሁንም በተጨማሪ፡ ወዳጆች ሆይ፡ መውጣት የሚገባችሁ ብዙ ሰዎች አላችሁ። እንዲህ በመጥራት፡ ላሳፍራችሁ አልፈልግም። ትክክልም አይደለም። ምናልባት ፍቃዳችህ ከሆነ... ፈሪሳውያን ድነናል ብለው ያሰቡ ነበር፡ ይሁን እንጂ አልዳኑም። እናንተም ያንኑ ታስባላችሁ። አሁን ኑ።

207 እርግጠኛ ሁኑ! በፍጹም፡ ግማሽ መንገድ እድል ፈንታ አትውሰዱ። በአእምሯችሁ ውስጥ ትንሽ ጥርጣሬ ካለ፡ እድል ፈንታ አትሰጡት። አሁን ኑ። መንፈስ ቅዱስ እዚህ እያለ፡ ምንጩም ተከፍቶ ባለበት፡ ጊዜው አሁን ነው። መምህሩ መጥቷል። ስለ ትንሿ ጥርጣሬህ፡ "ትጠራጠራለህ፡" እና አቁም። ሊላችሁ ፈልጓል። ኑ፡ አሁን። መምህሩ መጥቷል ይጠራችሁማል። አዎን፡ መምጣታችሁ ቀጥሉ፡ መምጣታችሁን አታቁሙ።

> አመሰግነዋለሁ፡ አመሰግነዋለሁ፡ (መጥታችሁ ክብር ትሰጣላችሁን? )
> ስለ ኃጢአተኞች የታረደውን በግ አመሰግኑ፡
> ሰዎች ሆይ፡ ሁላችሁ ክብር ስጡት፡
> ደሙ ዝገትን ሁሉ አሰወግዷልና።

208 አሁን ኃጢአተኞቹ፡ እሱን ለመቀበል እየወጡ፡ አሁን እየዘመርን፡ ህዝብ ሁሉ ምስጋና ያቅርብለት። አሁን ሁላችንም በአንድ ላይ፡ እጆች ይነሱ፡ እሱን ለማወደስ እንዘምር።

> አመሰግነዋለሁ፡ አመሰግነዋለሁ፡
> ስለ ኃጢአተኞች የታረደውን በግ አመሰግኑ!

209 በቃ አመሰግኑት! እዚህ ጋር ያላችሁ ሰዎችም፡ ጸልዩ፡ ይቅር በለኝ በሉት። እሱም ይተውላችኋልና። መምህሩ መጥቷል ይጠራችሁማል። ጌታ ይባርካችሁ።

**ኢየሱስም መጣና ጠራ** AMH64-0213

(Then Jesus Came And Called)

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ የካቲት 13፡ 1964፡ ሐሙሰ ማታ፡ በቱለር፡ ካሊፎርኒያ፡ ዩ ኤሰ ኤ፡ ከሚገኘው ኤልየት አዳራሽ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይሰ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግሰ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2022 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org